# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
# የሕፃናት እና የቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት
# /ኢ.ኦ..ቤ.ክ.ሕ.ቤ.ጉ.ድ/

## የራስ አገዝ ቡድኖች /ራአቡ/ በከፍተኛ ደረጃ ያለ ጥምረት (CLA) /ራአቡ ፌደሬሽን ድርጅታዊ መመሪያ

በየም አማካሪዎች ተቋም የተዘጋጀ

ታሕሳስ 2004 ዓ.ም.

## መግቢያ፡ የራስ አገዝ ቡድን  ስልት እይታ

## ክፍል አንድ

## የራስ አገዝ ቡድን /ራአቡ/ ድርጅታዊ መመሪያ

## ምእራፍ 1፡ የራስ አገዝ ቡድን (ራአቡ) መዋቅርና የስራ ስልት

## 2.1 ራስ አገዝ ቡድን /ራአቡ/ ምን ማለት ነው

ራስ አገዝ ቡድን /ራአቡ/ ማለት በጥቂቱ ራሣቸውን የሚያስተዳድሩ ለፖለቲካ ያልተሰባሰቡ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ በተለይም ተመሣሣይ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚአዊ የኑሮ ሁኔታ ያላቸው እና የጋራ ጉዳዮች ያሏቸው በፈቃደኝነት የተሰባሰቡ ለጋራና ለግል፣ ለማህበራዊና ለኢኮኖሚያዊ እድገት የሚሰሩ ናቸው፡፡ ሁሉም አባላት በቀጥታና በተሟላ ሁኔታ በቡድኑ ተግባሮች ውስጥ ይሣተፋሉ፡፡ የራስ አገዝ ቡድን ትንንሽ ቁጠባዎችን በአባላቱ ውስጥ ያበረታታል፡፡ ቁጠባዎቹ በባንክ ውስጥ ይቀመጣሉ፡፡ ይህ የጋራ ገንዘብ የሚቀመጠው በራስ አገዝ ቡድኑ ስም ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የራስ አገዝ ቡድን አባለት ቁጥር ከ15 እስከ 20 የሚደርሱ ሴቶች ናቸው፡፡

## 2.2 ራስ አገዝ ቡድን የማቋቋም አላማዎች

በመህበረሰቡ እና በመንደር ደረጃ ተቋማዊ አደረጃጀት ለመገንባት ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸውና የራሣቸው አባላት ያሉአቸው ድርጅት እንዲያቋቋሙ እና ቀጥሎም ራሣቸውን በከፍተኛ ደረጃ በማደራጀት ብዙ ተግባራትን በራሳቸው ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲፈጽሙ ለማስቻል ነው ፡፡ እንደዚህ አይነቱ ማህበር ፌደሬሽን መፍጠር ጥሩ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ እንዲደርሱና በድርድር ወቅት የተሻለ ድምፅ እና ለራሣችን ደግሞ የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡

### 2.3 የራስ አገዝ ቡድን ግብ ማስቀመጥና ተልእኮ ማዘጋጀት

የቡድኑ አባላት ስልታዊ እቅድ እና በጊዜ የተወሰነ የተግባር እቅድ አዘግጅተዋል፡፡ እነዚህን እቅዶች ተግባራዊ ለማድረግ ተግተው ይሰራሉ፡፡ አንድ ጊዜ እቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ በሥራ ሂደት ውስጥ መሰራት ከጀመሩ ግቦችን ያስቀምጣሉ፡፡

ግባቹም ግልፅ፣የሚለካ፣ የሚደረስበት፣ ተማኝ እና በጊዜ የተወሰኑ መሆን አለባቸው (SMART)፡፡ ተባበር ራስ አገዝ ቡድን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካ አካባቢ የአጭርና የረጅም ጊዜ ግቦች አሉት፡፡ ግቦቹም የልማትና የማብቃት ናቸው፡፡

| የአጭር ጊዜ ግብ/1 አመት/ | የረጅም ጊዜ ግብ /3አመት/ |
|---|---|
| በኢኮኖሚ<br>- የቡድን ቁጠባ በእያንዳንዱ አባል 1000 ብር ይሆናል<br>- 6 አባላት የገቢ ማስገኛ ስራ እንዲጀምሩ ይበረታታሉ<br>- ከፍተኛ የብድር ጣሪያ ለእያንዳንዱ አባል 3000 ብር ይሆናል | በኢኮኖሚ<br>- የቡድን ቁጠባ በእያንዳንዱ አባል 3000 ብር ይሆናል<br>- ሁሉም አባላት የገቢ ማስገኛ ስራ እንዲጀምሩ ይነቃቃሉ<br>- ከፍተኛ የብድር ጣሪያ ለእያንዳንዱ አባል 8000 ብር ይሆናል<br>- |
| ማህበራዊ<br>- ሁሉም ለትምህርት የደረሱ የራስ አገዝ ቡድን አባላት ልጆች ትምህርት ቤት ይገባሉ<br>- የራስ አገዝ ቡድን ቡድናቸውን በማህበረሰቡና ማህበራዊ ተግባር ኘሮግራሞች ላይ በመሣታፍ አጋጣሚዎችን ይፈልጋሉ<br>- የራስ አገዝ ቡድን አባላት ሕፃናት ልጆች የሚሠሩት ከፍተኛ ስራ ይቀንሣል<br>- የራስ አገዝ ቡድን አባላት የትምህርት ደረጃና ግንዛቤ ይጨምራል | ማህበራዊ<br>- ሁሉም ለትምህርት የደረሱ የራስ አገዝ ቡድን አባላት ልጆች ትምህርት ቤት እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ይገባሉ<br>- 50% የሚሆኑ ሁሉም አባላት በመሀበረሰብ ኘሮግራም ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ<br>- የቡድኑ አባላት ልጆቻቸውን በማህበራዊ ኘሮግራም ውስጥ እንዲሣታፉ ያበረታታሉ<br>- የሴቶች ጤና ትምህርት እና የሕፃናት መብቶች ይሻሻላሉ፡፡ የሕፃናት አስገድዶ መደፈር ይቀንሣል |
| ፖለቲካ<br>- የራአቡ ፆንሰ ሀሣብ ለመሃበረሰቡ መሪዎች ማስተዋወቅ እና ለፅንሰ ሃሣብ የተሻለ መረዳት እንዲኖራቸው ይረዳል | ፖለቲካ<br>- የራስ አገዝ ቡድንን ፅንሰ ሃሣብ ወደ ከፍተኛ ክልል ደረጃ መውሰድ<br>- የራአቡ አባላት የፓለቲካ ሁኔታውን ለመገንዘብ እንደረዳቸው በኮንፍረንሶች |

| | |
|---|---|
| - በተደጋጋሚ ወደ የማህበረሰብ መሪዎች ፍርድ ቤት ቢሮ ጉብኝት የማድረግ ጥረት እና ትስስር መፍጠር የሚቻልበት ሁኔታ ማሳየት | ላይ ይሣተፋሉ |

አባላት ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ልማት የየራሣቸውን ግብ እንዲያስቀምጡ ይበረታታሉ፡፡ እነዚህ ግቦችና እነሱን ለማሣካት ያለው ሂደት በሣምንታዊ ስብሰባ ላይ ከሌላ አባላት ጋር ልምድ ይለዋወጡባቸዋል፡፡ ይህም አባላት አንዱ ሌላውን በመርዳት የጋራ እድገት እንዲያመጡ ያግዛቸዋል፡፡

ቡድኖቹ በየስድስት ወሩ የራሳቸውን ቡድን ሁኔታ እንዲገመግሙ ይበረታታሉ፡፡ አሣታፊ የነጥብ መስጫ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ አባላቱ የሚገመገሙበትን አካባቢ ይወስኑና በ5 ነጥብ መለኪያ ደረጃ ይወጣላቸዋል፡፡

## 2.4 የ ራስ አገዝ ቡድን የሥራ መርሆች

ሀ/ **ትንሽ ቡድን፡** ሁሉንም አባላት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማሣተፍ ፅንሰ ሃሣብ የትንሽ ግሩፖችን ምስረታ ያበረታታል፡፡ ባጠቃላይ ከ15-20 አባላት ያሏቸው ብድኖች ውጤታማ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ የአንድ ቡድን አባላት ከ20 መብለጥ የለበትም

ለ/ **ተመሣሣይነት** አባላቱ በተመሣሣይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የተገኙ ከሆነ፣ አንድ አይነት አጀንዳ ካላቸው እና ተፈጥሮአዊ መቀራረብ ካላቸው በአንድ ግሩኘ ሆነው ለመስራት በጣም ይቀላቸዋል፡፡

ሐ/ **ተግባራዊና ሙሉ ተሣትፎ፡-** ቡድኑ ቋሚ በሆነ መንገድ መሠብሰብ አለበት ቢያንስ ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ ፡፡ ሁሉም አባላት ሁሉም ስብሰባዎች ላይ መገኘት አለባቸው፡፡

መ/ **ነፃነት**፡ ቡድኖቹ በተግባራቸው ነፃ ናቸው፡፡ በራሳቸው ሕግ፣ መመሪያዎችና ደንቦች መሠረት ይንቀሣቀሣሉ፡፡ በተፈጠረው ጉዳይ ላይ መሠረት በማድረግ

ሁሉም አባላት በጋራ በመሰባሰብ በመመሪያዎችና በሕጐች ላይ ይወሰናሉ ቡድኑ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ለራሱ ኃላፊነት ይወስዳል።

ሠ/ **በጋራ የሚመራ፡-** ምንም እንኳን ቡድኑ ተወካዮች፣ የሚደግፉ እና ገንዘብ የኘር ቢኖሩትም ውሣኔ በማያስተላልፉበት ወቅት የቢሮ ሠራተኛው ምንም አይነት ጣልቃ አይገባም። ሁሉም ውሣኔዎች በቡድኑ ስብሰባ ጉዜ ሁሉም አባላት ባሉበት ይተላለፋል። ሁሉም ውሣኔዎች ስለዚህ በስምምነት ይተላለፋሉ። ቢሮውን የሚያስተዳድረው ሠው የኃላፊነት መገለጫ ነው እንጂ እንደ ወሣኝ ሀይል አይታይም። ይሁንና የቢሮው አስተዳዳሪነቱ በቋሚነት በዙር የሚደርስ ሲሆን ይህም ስልጣን በጥቂቶች እጅ እንዳይሰባሰብ ለማስወገድ ይረዳል።

ረ/ **አባልነት በፈቃደኘነት፡** በተገለፀላቸው ጽንሰ ሃሣብ መሠረት ቡድኑ በራሱ የተመሠረተ ነው። የቡድኑ አባልነት የሚወሰነው ወደፊት አባል በሚሆኑት እና በሌሎች የቡድኑ አባላት መካከል ነው እንጂ በሌላ በማንም አይደለም። ቡደኑ ብራስ ምርጫ መሠረት ይመሰረታል። አባላት እርስ በራሳቸው ተመራርጠው የቡድኑን አባልነት ያጠናቅቃሉ፡

ሰ/ **መረዳዳት፡** በጋራ መረዳዳት የራስ አገዝ ቡድን በግል፣ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ የአባልነት ልማት ጥረት ያደርጋሉ።

ሸ/ **ቋሚ ቁጠባ፡** በጋራ ለመረዳዳት የራስ አገዝ ቡድን በቡድርና ቁጠባ ስራዎች ላይ ትኩረቱን ያደርጋል። ቁጠባ ከትርፍ አይደለም ነገር ግን አባላት ከፍጆታቸው ላይ የቱንም ያክል ትንሽ ብትሆን ማስቀመጥ አለባቸው። የቡድኑ አባላት በጋራ የቁጠባውን መጠን አና በምን የክል ጊዜ እንደሚቆጥቡ ይወስናሉ።

## 2.5 የራስ አገዝ ቡድን ድርጅታዊ መዋቅር

የራስ አገዝ ቡድን ውሣኔ ሰጪ አካል ጠቅላላ ጉባኤው ነው። ጠቅላላ ጉባኤ ----- አባላት አሉት ሁሉም የራስ አገዝ ቡድን አባላት /የድርጅቱን መዋቅር ተመልከተ/። በዲሞክራሲያዊ አሠራር ሂደት ጠቅላላ ጉባኤው የተለያዩ የራስ አገዝ ቡድን ስራ አስፈፃሚዎች ይመርጣል




-------- የስራ ግንኙነት

የተለያዩ የስራ አስፈፃሚ አካላት ምርጫ በተወሰኑ መስፈርቶች ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ጥሩ የስራ አስፈፃሚ ባሕርያት ፣ ሚና እና ኃለፊነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ የራስ አገዝ ቡድን ተወካዮች ባህርያትና ሚና

**የጥሩ ተወካይ በህርያት**

- ትክክለኛ መረጃዎችን ከአባለት ወደ ሌላ ፎረሞች እና ከሌሎች ወደ አባላት ማድረስ
- በአካባቢ ስላሉ ሁኔትዎች እውቀት እና ግንዛቤ ያለው እና ራሱን በመረጃ የሚያጠናክር
- የሚያነሣሣ/የሚፈጥር
- መሰጠት

**የተወካዮች ሚና**

- ሳምንታዊ ስብሰባዎች በተከታታይ መካሄዳቸውን ማረጋገጥ
- በቡድኑ አባላት መካከል ጥሩ ግንኙነት ለማሣለጥ እና የራስ አገዝ ቡድኑ በጥሩ ሁኔታ እየሠራ መሆኑን ለማረጋገጥ
- አባላት በራስ አገዝ ቡድን ያለመግባባት ሊፈጠር ቢችል ችግሩን እንዲፈታ ለማሣለጥ

- በራስ አገዝ ቡድን  እና በሌላ ተቋማት ውስጥ ግንኙነት ለመፍጠር
- ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከስልጠና እና ከውጭ ግንኙነት የተገኙትን ለሌሎች የራስ አገዝ ቡድን አባላት ማካፈል
- በቡድኑ ስልጣን በተሰጣቸው መሠረት በጋራ የባንክ ሂሣቡን ለማንቀሳቀስ
- የራስ አገዝ ቡድን  የገንዘበ ጉዳዮችን ለመከታተል የመዝገብ አያያዝን፣ የሂሂብ ምርመራን እና የገንዘብ አስተዳደርን ጭምሮ
- ከመፈረም በፊት የተወሰዱ ውሣኔዎችን በቃለ ጉባኤ ላይ ማረጋገጥ
- የራስ አገዝ ቡድን  በሌላ ፎርሞች ላይ መወከል
- የራስ አገዝ ቡድኑን ውሣኔ ቡድኑ እንዲተገበር ማሣለጥ
- ለራስ አገዝ ቡድን  ጥቅም የአካባቢን ሀብት ለማሰባሰብ መሞከር

## ለ/ የራስ አገዝ ቡድን  መዝገብ ፀሐፊ ባሕርያትና ሚና

### የመዝገብ ፀሐፊ ባሕርያትና

- በመሃበረሰብ ውስጥ ያለና ታዋቂ
- ቡድኑን መምራት የሚችል
- ታማኝና ጉበዝ
- ታጋሽ፣ በተፈለገ የሚገኝ፣ ጥሩ አስተሳሰብ ያለው
- የተማረ
- ለመማር ዝግጁ የሆነና የተማረችውን /የተማረውን ለሌሎች አባለት የሚያስተላልፍ
- ንፁሕ እና መዝገቦችን ጥሩ አድርጎ የሚይዝ
- የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን በጥሬ ገንዘብ መዝግብ ላይ መመዝገብ የሚችል

### የመዝገብ ፀሐፊ ሚና

- ሁሉም የሂሣብ መዝገቦች ወቅታዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ
- በቁጠባ ደብተሩ ላይ የሁሉንም አባላት ቁጠባ መመዝገብ
- የተሰበሰበውን የቁጠባ መጠን በጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ ላይ መመዝገብ
- የተከፈለውን ብድር መጠን በጥሬ ገንዘብ መዝገብ ላይ መመዝገብ
- በጥሬ ገንዘብ መዝገብ ላይ የተሰበሰውን ክፊያ መጠን መመዝገብ
- መዝገቦች እና ማስረጃዎች በጥሩ ሁኔታና በጥሩ ቦታ መቀመጣቸውን እና በተፈለጉ ሰአት እንዲገኙ ማረጋገጥ
- የራስ አገዝ ቡድን ገንዘብ መመርመሩን ለማረጋገጥ
- ስልጠና በተዘጋጀበት ጊዜ ስልጠና መካፈል
- ሁለተኛ የመዝገብ ያዥ መስመር በራስ አገዝ ቡድን መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ
- ወርሀዊ ሪፖርቶች ለማዘጋጅት እና ለአባላት ለጥምረቱ እና ለ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ማቅረብ
- ለራአቡ አባላት የትምህርት እና የቁጥር ክሕሎት እንደያሻሽሉ መስራት
- አባላትን በባንክ የገንዘብ ዝውውር ማሰልጠን

ሐ/ የብዙ በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት ሚና

| የጥሩ ተወካይ ባሕርያት | የጥምረቱ ተወካዮች ሚና |
|---|---|
| - ጠንካራ ባሕሪ ያላት ሴት<br>- ተግባቢ<br>- በመህበሩ ውስጥ ያለችና ጐልታ የምትታይ<br>- ቡድን መምራት የምትችል<br>- ታማኝና ጉበዝ | - ሁሉንም ስብሰባዎችና ሥልጠናዎች ለመከታተል<br>- ለራአቡ አባለት ስለ የራአቡዎች ከፍተኛ ጥምረት ማስተዋወቀ እና ግንዛቤ መስጠት<br>- በራአቡ አባላት የማይፈቱ ችግሮች ጉዳይ ለመለየት እና በጥምረቱ ድጋፍ ለመፍታት መሞከር<br>- በማመልከቻ ትክክለኛ ፍሰት እና ሌሎች ፈንዶችን በራአቡ እና በጥምረቱ ለማረጋገጥ<br>- ትክክለኛ የጥምረቱ በድር ክፍያን ማረግገጥ<br>- ደካማ የራአቡ አባላትን ለመጉብኘትና በቃታቸውን ማነቃቃት<br>- ኤኤጅን ለማሣተፍ እና በየጊዜው ጥናት ማድረግ<br>- ቃለጉባኤዎችን በትክክል መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ<br>- በራስ አገዝ ቡድናቸው ውስጥ ስላለ ውጤትና ድክመት ለጥምረቱ አባላት ልምድ ማካፈል |

## 2.6 በራስ አገዝ ቡድን የአመራር ሁኔታ

በማንኛውም ጊዜ ከአንድ ግለሰብ በላይ የሆኑ ሰዎች ለተወሰነ አለማ ከተሰባሰቡ አመራር አስፈላጊ ይሆናል። የቤተሰብ ጉዳይ ይሁን፣ የአቻዎች ቡድን ተግባር ወይም የሕዝብ አስተዳዳር ለዚህ ሁሉ አመራር አስፈላጊ ነው። አመራር በሚያስፈልገው ጉዳይ በሁኔታው ተፈጥሮአዊ ባሕሪና በተግባሩ ላይ ተመስርቶ

የአመራሩ ዘዴ ይለያያል፡፡ ራስ አገዝ ቡድኖችን በተመለከተ ግን የጋራ አመራር ይበረታታል፡፡ በቡድኑ ውስጥ የሚተላለፉ ሁሉም ውሳኔዎች በአባላቱ አጠቃላይ ስምምነት ነው፡፡ ቡድኑ በጋራ ለሚወስዱአቸው ውሣኔዎች ሃላፊነትና ተጠያቂነቱን ይወስዳሉ፡፡ ይሁንና የቡድኑ አንዳንድ ሥራዎች በጥሩ ሁኔታ ይከናወኑ እንደሆነ ለማየት እያንዳንዱ ቡድን ሶስት የቢሮ ሠዎች ያስፈልጉትል ከላይ እንደተገለፀው በስም ተወካዮች፣ መዝገብ ያዥና የጥምረቱ ተወካዮች ናቸው፡፡

እነዚህ የስራ ኃላፊነቶች ከስልጣን ይልቅ ኃላፊነታቸው ይበዛል፡፡ የቡድን ተወካዮች ብቻቸውን ምንም አይነት ውሣኔዎችን እያስተላልፊም ምክንያቱም በራስ አገዝ ቡድን አመራር ውስጥ ስምምነትን መሠረት በማድረግ ብቻ ውሳኔ ስለሚተላለፍ ነው፡፡ ሁሉም ውሣኔዎች የሚተላለፊት ቢያንስ ቢያንስ ከ80 በመቶ በላይ የቡድኑ አባላት በተገኙበት ስብሰባ ነው፡፡ ቡድኖች የቡድን መሪዎቻቸው ለምን ያክል ጊዜ እንደሚያገለግሉ በራሣቸው ይወሰናሉ፡፡ ነገር ግን ስልጣን በተወሰኑ ሠዎች እጅ ውስጥ መሠባሰብን ለማስወገድ መሪዎችን በየጊዜው መቀያየር ይበረታታል፡፡ በቡድኑ የተመረጡ ሠዎች ብቻቸውን ውሣኔ ማስተላለፍ እንዳይችሉ መመሪያ ማውጣት አለባቸው፡፡

## 2.7 የአባላት ሚና እና ኃላፊነት

ዋና ዋና የ ራስ አገዝ ቡድን አባላት ሚና እና ኃላፊነቶች

- በቡድኑ ስብሰባ ላይ በቋሚነት መሣተፍ
- በቡድኑ ስብሰባ ላይ በጥሩ ሁኔታ ለመሣተፍ እና ሃሣብን በግልፅና በነፃነት መግለጽ
- የስልጠና ኘሮግራሞች ላይ በስርአት መከታተል
- ከሁሉም የራስ አገዝ ቡድን  አባላት ጋር ችግሮችን፣ ልምዶችን እና ኀሣቦችን መካፈል
- በየሣምንቱ በቡድን አባላት ስምምነት የተደረሰበትን ትንሹን ቁጠባ መቆጠብ
- ለእያንዳንዱ የራስ አገዝ ቡድን ስብሰባ ላይ የአባልነት ደብተር በማምጣት ወቅታዊ መረጃ መያዝ

- ለትክክለኛ ጉዳይ ብድር መውሰድ እና ብድርን ላልተፈለገ አላማ ያለማዋል
- የራስ አገዝ ቡድን  ብድር ከነወለዱ በስርአት መክፈል
- ሁሉም የቡድኑ አባላት የወሰዱትን ብድር ስምምነት ለተደረሰበት ተግባር ማዋላቸውን ማረጋገጥ
- ብድራቸውን በሰአቱ ይከፈሉ እንደሆነ ለማረጋገጥ
- የገንዘብ እንቅስቃሴአቸውን ከራስ አገዝ ቡድን ጋር በስብሰባ ጊዜ ብቻ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ
- የራስ አገዝ ቡድን ኃላፊነትን በጋራ መውሰድ፡፡ ለምሣሌ ባንክ በተራ መሄድ
- የተወካዮችን በዙር መቀያየሩን ለማረጋገጥ
- በማህበረሰቡና/በማህበረሰቡ የጋራ ስራ ላይ መሣተፍ

## 2.8 ዋና ዋና የራስ አገዝ ቡድን ተግባራት

ዋና ዋና የራስ አገዝ ቡድን ተግባራት በሚከተሉት ስራዎች ላይ ያተኩራል

- በየሣምንቱ መገናኘት
- በስብሰባ ወቅት መቆጠብ
- በስብሰባ ወቅት በጉዳዮች ላይ መወያየት እና ውሣኔ ማሣለፍ
- ብድር ማስተዳደር
- የብድር አጠቃቀምን መከታተል
- የብድር በትክክለኛ ሁኔታ መክፈልን ማረጋገጥ
- የሚያስፈልገውን የሂሣብ መዝገብ መያዝ
- ከመንግስት ክፍሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር
- የስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ኘሮግራሞችን ማዘጋጀት
- ለሌሎች የራስ አገዝ ቡድኖች የልምድ ልውውጥ ማዘጋጀት
- በመንደር ውስጥ የመሃበረሰብ እና የማህበረሰብ የጋራ ስራ ማነሣሣት
- ብድርና ስራ ማነሣሣት
- የገቢ ማስገኛ ስራ ማነሣሣት

## ምዕራፍ 2

## የውስጥ የስራና የተግባር መመሪያዎች

2.1የውስጥ ስራቸውን በስልታዊ መንገድ ለማከናወን ራስ አገዝ ቡድን በስምምነት መመሪያዎችን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የተዘጋጀውን መመሪያ ሁሉም አባላት በመከተል የቡድኑን አላማ ለማሣካት ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

2.2እያንዳንዱ የቡድን አባል የተለያየ ሁኔታና ፍላጐት አለው ቢሆንም በቡድን ውስጥ ሁሉም አባላት በቡድን መንፈስ መስራታቸው አስፈላጊ ነው በዚህ መንግድ ብቻ ነው የቡድን አለማ ሊሣካ የሚችለው፡፡ በዚህ መንፈስ የቡድኑ መመሪያዎች ይዘጋጁና በሁለም አባላት ላይ እኩል ይጠላሉ፡፡ መመሪያ የስራ አሰራርን እና የኃላፊነት ሚናን በእያንዳንዱ አባል ላይ ያረጋግጣል፡፡

2.3በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ/በሳምንታዊ ስብሰባ ላይ በሁሉም አባላት ስምምነት በስብሰባው አባላት በቃለ ጉባኤ መዝገብ ላይ በማስፈር መመሪያዎች መተግባራቸውን መፈረማቸውን እና በሚከተለው መንገድ ይሆናሉ

አባላት ለቡድናቸው ቀላል መመሪያ እንዳያዘጋጁ ይበረታታሉ፡፡ እነዚህን መመሪያዎች በመፃፍ ህጋቸው አድርገው ይከተሏቸዋል፡፡ አባላት የራሣቸውን መመሪያዎቻቸውን እና ሕጐቻቸውን በቃለ ጉባኤ መዝገባቸው የመጀመሪያ ገጽ ላይ ያሰፍሯቸዋል፡፡ መመሪያዎቹ በጣም መሠረታዊ ናቸው፡፡ ወደ ስብሰባው በቋሚነት ስለመምጣት፣ ወደ ስብሰባው በሰአት ስለመድረስ፣ በቋሚነት ስለመቆጠብ እና እርስ በእርሳቸው ስለመከባበር ያወራሉ፡፡

ሀ/ **ከስብሰባ ጋር የተያያዙ መመሪያዎች፡-** በተባበር ስር የተቋቋሙ ራስ አገዝ ቡድን ሳምንታዊ ስብሰባ ማካሄድ ግዴታቸው ነው፡፡ የስብሰበ ቀን፣ሰአት እና ቦታ በስምምነት መወሰንና ሁሉመ በተቻለ መጠን በስብሰባ ላይ እንዲገኙ መቀራረብ አለባቸው

ለ. **በስብሰባ ላይ ከመገኘት ጋር የተያየዙ መመሪያዎች፡** ሁሉም አባላት በስብሰባ ላይ መገኘት የግድ ነው፡፡ ምናልባት አንድ አባል በስብሰባ ላይ የማይካፈልበት ሁኔታ ቢፈጠር ቀድሞ ምክንያቱን በመግለጽ ማሣወቅ አለበት፡፡ ምናልባት አንድ አባል ቀድሞ ሳያሣውቅ ከስብሰባ ቢቀር ወይም አርፍዶ ቢመጣ የዚህ አይነት አባል ቅጣት ይከፈላል፡፡ ለቅጣቱ የቡድኑ አባላት ስንት ሊሆን እንደሚችል ይወስናሉ፡፡ የቅጣት ክፍያው ዝቅተኛ መሆን ይኖርበታል ይህም ሁሉም አባላት እንዲከፈሉ ያስችላቸዋል፡፡

ሐ. **ከአዳዲስ አባላት እና ከቡድን የሚባረሩ አባላት ጋር ተያይዞያ ያሉ መመሪያዎች**

ቡድን፡- ቡድኑ አባላትን ለማባረር መመሪያ ሊያዘጋጅ ይችላል፡ ምን አልባት አባላት ከቡድኑ ለመልቀቅ ከተቀመጠው ዝቅተኛ ጊዜ ቀድመው ቢለቁ ያጠራቀሙትን ቁጠባ የተወሰነ መጠን ቡድኑ ይወስዳል፡፡ ምናልባት ማንኛውም አባል ቡድኑን በማንኛውም ጊዜ ቢለቅ በዚያ ጊዜ ውስጥ ያለውን ትርፍም ይሁን ኪሣራ እኩል ይካፈላል፡፡ በተመሣሣይ ቡድኑ 20 እስኪሞላ ድረስ አዳዲስ አባላትን ለመቀበል መመሪያ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ አዳዲስ አባላት የቀድሞ አባላት የቆጠቡትን ያክል ገንዘብ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም አዳዲስ አባላት ለሌሎች አባላት ለግዥ ያውጧቸውን ለጥሬ ገንዘብ ሣጥን ፣ ለሂሣብ መዝገብ እና ለሂሣብ መዝገብ መክፈቻ ወዘተ ያወጡትን ወጪ ማውጣት አለባቸው፡፡ ምናልባት ቡድኑ አንድን አባል ማባረር ቢፈለግ ማናቸውም አይነት ውሣኔ ሣይወሰድ አባሉ እንዲሰማ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

መ. **ከቁጠባ ጋር የተያየዙ መመሪያዎች** ፡- አባላት የሚቆጠበውን መጠን በጋራ ስምምነት ይወስናሉ፡፡ የቁጠባ መጠኑ ሁሉም አባላት በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ መቆጠብ የሚችሉት መሆን አለበት፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሁሉም አባላት ከተስማሙ ቡድኑ የቁጠባውን መጠን ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡ በማንኛውም ስበሰባ ላይ ማንኛውም አባል ቁጠባዋን ሳይከፍል ከቀረ በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ ማንኛውም አባል

ቁጠባውን መክፈል አለባት ። ቡድኑ ዘግይተው በሚከፋሉ አባላት ላይ ቅጣት ማስከፈል ከፈለገ መመሪያ ማዘጋጀት ይችላል። ከቁጠባው የቡድኑን የፅሁፍ መረጃ ይሠራል።

ሠ/ **ከብድር ጋር የተያያዙ መመሪያዎች**። ከፍተኛና ዝቅተኛ የብድር ጣሪያን በቡድኑ መወሰን። ከተቀማጭ ገንዘብ ላይ ለአባላት ብቻ ብድር መስጠት፡ ዘግይቶ ብድር ለሚከፍሉ ሠዎች ቅጣት መወሠን። ማንኛውም መጠን ያለው ገንዘብ ቅጣት ሊወሰን ይችላል። ሁለት አይነት ብድሮች ሊኖሩ ይችላሉ።

I. **በአንድ ጊዜ የሚከፈል፡-** ብድር በሚወሠድበት ወቅት ተበዳሪው በተወሰነ ጊዜ ውሰጥ ብዱሩን ለመመለስ እቅድ ሊያቀርቡ ይችላል። በዚህ አይነት ብድር አባላት ብድሩን አንድ ጊዜ ለመክፈል ሁኔታዎች ይመቻቹላቸው እና ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ሌሎች አባላት ያንን መጠን ለመክፈል አይጠበቅባቸውም።

II. **የብድር ክፍያ ሁኔታ፡-** በዚህ አይነት ብድር ተበዳሪዎቹ ብድሩን በሚወስዱበት ጊዜ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እኩል በሆነ የብድር አከፋፈል ሁኔታ ስለመክፈል የሚገልፅ እቅድ ያቀርባሉ። በየተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የብድር አከፋፈል ሁኔታ ብድሩ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ የብድር ክፈያው ይጀምራል።

ረ. **የወለድ መጠንን በተመለከተ መመሪያ፡-** አንድ ቡድን የወለድ መጠን ሲወሰን በአካባቢ ካሉ ገንዘብ አበዳሪዎች ከሚጠይቁት ወለድ ያነሰ እና ምናልባት ደግሞ ከባንክ ወለድ በላይ አድርገው ይወስናሉ። ምናልባት አባላት በተወሰነላቸው ጊዜ ውስጥ ብድራቸውን መክፈል ባይችሉ በቀሪው ብድር ላይ ተጨማሪ ወለድ እንደቅጣት ሊጣልባቸው ይችላሉ። ቡድኑ በሚከተለው መንገድ መመሪያውን ሊያዘጋጅ ይችላል።

I. ምናልባት ቡድኑ በማንኛውም ሰአት ወለድ ቢጨምር ይህ ሁኔታ ተገባራዊ የሚሆንባቸው አባላት ጭማሪው በተደረገበት ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ ብድር በወሰዱት ላይ ነው።

II. ምናልባት ስበሰባ በተወሰነ ጊዜ ሳይካሄድ ቢቀር ምንም እንኳን ለአባላት የወለድን መጠን ማላላት ባይኖር፡፡

III. በብድር መመለስ ጊዜ መጀመሪያ ወለድ ሲከፈል ቀጥሎ ደግሞ ዋናው መጠን ይከፍላል፡፡

IV. ምናልባት ከአባላት መካከል አንድ ሰው በሞት ከቤተሰቦቹ ለአንዱ የቡድኑ አባል እንዲሆን ይፈቀድ እና እሷ/እሱ የተወሰደውን ብድር ለመክፈል ኃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡

V. የቁጠባ ወለድ፡- በቁጠባ ላይ ምንም አይነት ወለድ አይከፈልም

ሰ. **ለተለያዩ ኃላፊነት የተመረጡ አባላት የስራ ጊዜ ጋር የተያያዙ መመሪያዎች፡-** ለተለያዩ ኃላፊነት የተመረጡ የስራ ጊዜ ገደብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ የተወካዮች የስራ ጊዜ አንድ አመት ሲሆን የመዝገብ ያዦችም ከዚሁ ጋር ተመሣሣይ ሊሆን ይችላል፡፡ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተወካዮች የስራ ጊዜ ሁለት አመት ሊሆን ይችላል፡፡ የነዚህ የጥምረቱ የስራ ጊዜ ሁለት አመት ሊሆን ይችላል፡፡ የነዚህ የጥምረቱ ተወካዩች ስራ አጥጋቢ ሆኖ ከተገኘ የስራ ጊዜአቸው ለተጨማሪ አንድ አመት ሊራዘም ይችላል፡፡ ምናልባት አንድ ሰው የተሰጠውን ኃላፊነት ሳይወጣ ቢቀር በጠቅላላ ጉባኤው ስምምነት ይህን ሰው የስራ ጊዜው ከማለቁ በፊት ከኃላፊነት ሊነሣ ይችላል፡፡

ሸ. **ውሣኔ ከማሳለፍ ጋር በተያያዙ ያሉ መመሪያዎች፡-** ሁሉም በቡድኑ ውስጥ የሚተላለፉ ውሣኔዎች በሁሉም አባላት ስምምነት መሠረት ነው፡፡ ምንም እንኳን ሰማኒያ በመቶ የሚሆኑ አባላት በትንሹ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ውሣኔ ለማስተላለፍ መገኘት የግድ ይኖርባቸዋል፡፡

ቀ. **ብድር ክፍፍል ወቅት የሚሰጥባቸው መመሪያዎች፡-** ቡድኑ የትኛው ስራ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ይወስናል፡፡ አባሉ በሚያቀርበው የብድር እቅድ ውሰጥ የሚበደርበትን ምክንያት፣ የሚበደረውን መጠን እና የሚከፍልበትን ጊዜ እና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚከፈለውን መጠን ማካተት አለበት፡፡ የብድር እቅዱን ከመቀበላቸው በፊት ቡድኑ ፍላጐቱን እና የብድር መክፈል አቅሙን ይመረምር እና ትክክለኛ ሆኖ ሲያገኘው የብርድ መክፍያ ጊዜ ይወሰንለታል በዚህ መሠረት የተበደረው አባል የብድን መጠን በተቀመጠለት

ጊዜ ውስጥ መክፈል ይችላል ማለት ነው። ምናልባት ተፈጥሮአዊ በሆነ ችግር፣ በአደጋ ወይም በጤና ችግር ምክንያት አባሉ የወሠደውን ብድር በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ መክፈል ሳይችል በቀር በዚህ ጊዜ እሷ/እሱ ለቡድኑ ጥያቄ በማቅረብ ቡድኑ የብድር መክፈያውን የጊዜ ሁኔታ ሊቀይርለት ይችላል።

በ. **የስነ ምግባር መመሪያ**፡- የስነ ምግባር መመሪያ አላማ ለመቅጣት ወይም ገቢን ለመጨመር ብቻ አይደለም። ግለሰቡ ለቡድኑ ታማኝ እና ፍቅር እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ቅጣት አንድን ሰው ለቡድኑ እና ለሚሠራው ስራ ታማኝና ኃላፊነት ይሚሠማው እንዲሆን ያደርገዋል።

ተ. **የራስ አገዝ ቡድን የባንክ ሂሣብ፡-** ቡድኑ በቅርብ ባለ የመንግስት ባንክ የባንክ ሂሣብ መክፈት ያስፈልገዋል። የተመረጠ አባላት የባንክ ደብተሩን፣ የአባልነት ደብተሩን እና ሌሎች መረጃዎችን ይይዛሉ።

## 2.4 አርአያ የሚሆኑ የራስ አገዝ ቡድን ስብሰባ አጀንዳ

አንደ ቡድን በተወሰነ ቀን ስብሰባ ማዘጋጀት የግድ ይለዋል። ስብሰባው በአባላት ቤት ውስጥ በመዘዋወር ወይም በሌላ በሚመች ቦታ ሊደረግ ይችላል። የስብሰባ ግዜና ቦታ በስምምነት መወሰን አለበት እናም መረጃ ለሁሉም አባላት መሠጠት አለበት ይህ ካልሆነ ግን ሁሉም አባላት ወደ ስበሰባው ሊመጡ አይችሉም የሰብሰባ ጊዜና ቦታ ሊቀየር ይችላል ነገር ግን በቅድሚያ መረጃውን ለአባላት መስጠት አስፈላጊ ነው። የስበሰባው ሂደት ቀላል መሆን አለበት። የስብሰባው ሂደት የተለያዩ ደረጃዎች በገንዘብ ሁኔታ ላይ ሊያተኩር ይችላል ነገር ግን አላማቸው የኢኮኖሚ እድገት ይሆናል። የሚከተሉት ደረጃዎች ለቡድን ስበሰባ ተግባራዊ ይደረጋሉ።

**ደረጃ 1 ለስብሰባ ማነሣሣት**

ሀ. ቀድሞ በተወሰነ ቀን ፣ ሰአትና ቦታ አባላት ይሰበሰባሉ

ለ. ስብሰባው በሙዚቃ ወይም ቃል በመግባባት ይጀምራል

ሐ. ከዚህ በኋላ አንድ አባል መመሪያውን አንድ በአንድ ያነባል ሌላው አባል ደግሞ የሚነበበውን ይደግማል

መ. ሁሉም አባላት ክብ ሠርተው ይቀመጣሉ፣ ምን አልባት መዘገብ ያዥዋ የቡድኑ አባል ካለሆነች በስብሰባው መሣተፍ የግድ ይላታል

ሠ. የገንዘብ ሳጥን እና መመዝገቢያ ደብተሩ መካከላቸው ይቀመጣል

ረ. የቀኑ የስብሰባ አመቻች ስብሰባውን ትከፍታለች፡፡ ምንም እንኳን ተወካዮቹ ስብሰባውን በተለምዶ በመሩም በእያንዳንዱ ስብሰባ ሁሉም አባላት አንድ አባል ስብሰባውን እንዲመራ ይመረጣሉ በዚህ የተነሣ ሁሉም አባላት ስብሰባ የሚመሩበትን አጋጣሚ ያገኛሉ የቡድኑ ተወካዮች የተመረጡ ስብሰባውን ስርአት ባለው መንገድ እንደያከናውኑ ይረዳቸዋል፡፡

**የመሪዋ ሚና**

- በሥብሰባው ሂደት ላይ ሁሉም አባላት መሣተፋቸውን ለማረጋገጥ
- በስብሰባው ውሰጥ ስነስርአትን ለማረጋገጥ
- የቀኑን የገንዘብ እንቅስቃሴ ለመያዝና ገንዘቡን ወደ ባንክ ለማስገባት
- በሚቀጥለው የራአቡ ስብሰባ ላይ ባንክ ያስገባችበትን ደረሰኝ ለማቀረብ
- በስብሰባው የቃለ ጉባኤ ደብተር ላይ ባንክ የተላለፊ ውሣኔዎች መስፈራቸውን ለማረጋገጥ

ሠ. ምናልባት መዝገብ ያዧ ብትቀር ቡድኑ አንድ ማንኛውንም የተማረ ሰው በመምረጥ እንዲጽፍ/ቃለ ጉባኤ እንዲያዝ በመወሰን ይሾማል፡፡

ረ/ መዝገብ ያዧ የስበሰባውን ቃለጉበኤ እና የተለያዩ ትንተናዎችን እንደ የቡድን ስም፡ የስበሰባ ቀን፣ የስብሰባ ተሣትፎ ማረጋገጫ፣ የቀሪነትን ምክንያት ወዘተ ትፅፋልች

ሰ. ሁሉም ውሣኔዎች በቡድኑ ስምምነት ይተላለፋሉ፡ ይሁንና ግልፅነትን እግዲኖር በትንሹ 60 በመቶ አባላት ውሣኔው በተላለፈበት ስብሰባ ላይ መገኘታቸው የግድ ነው፡፡

ሸ. ምናልባት የሚፈለገው አነስተኛ የአባላት ቁጥር ያላቸው ሠዎች የማይሣተፉ ከሆነ በዚህ አይነት ሁኔታ ውሰጥ የሚተላለፉ ውሣኔዎች ተቀባይነት የላቸውም ከ80 በመቶ ያነሱ አባላት ባሉበት ሁኔታ ስብሰባው መቀጠል

የለበትም፡፡ በዚህ ሁኔታ ቡድኑ ደረጃ ለማውጣት የሚያበቃውን ውጤት አያገኝም እና ከባንኮችና ከሌሎች አካላት ጋር ስራ ማካሄድ አይችልም

ቀ. አንድ አባል በተከታታይ ሶስት ስብሰባዎች ላይ ካለተገኘ ሌሎች አባላቶች ለምን እንደሆነ ምክንያቱን ለማወቅ መሞከር አለባቸው፡፡ ምክንያቱም አጥጋቢ ሆኖ ካላገኙት ለዚህ አይነቷ አባል ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡

**ደረጃ 2. በስብሰባ ውስጥ ውይይቶች**

አባላት ውይይታቸውን እንደትምህርት፣ ጤና፣ ውሃ እና ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ስለሆነም ሁሉም አባላት አሁን ስላለው ሁኔታ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸው እና ያለውን ሁኔታ ለማሻሻል አስተያየት መስጠት ይችላሉ፡፡ በዚህ አይነት ውይይቶች የአባላት እውቀት እና መረዳት ደረጃቸው ይጨምራል፡፡ከዚህ በኋላ አባላት ውሳኔ በሚጠጥባቸው ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ፡፡ መዝገብ ያዥ እነዚህን ውይይቶች እና የተላለፊ ውሣኔዎችን በቃለ ጉባኤው ላይ መፃፍ አለበት፡፡

**ደረጃ 3 የጥሬ ገንዘብ ማስማማት**

መዝገብ ያዥ የባለፈው ሣምንት የሂሣብ መዝገያ የነበረውን የዚህ ሣምንት የሂሣብ መክፍቻ በጥሬ ገንዘብ መመዝገበያው ላይ ትሞላለች፡፡ አንድ አባል በጥሬ ገንዘብ ሣጥኑ ውስጥ ያለውን ጥሬ ገንዘብ ከጥሬ ገንዘብ መዝገቡ ጋር እና በስብሰባ ቃለ ጉባኤ ላይ የተፃፈውን ታስማማለች፡፡ ከተስማማ በኋላ አባላት ጥሬ ገንዘቡን ወደ ጥሬ ገንዘብ ሣጥኑ ይምልሣሉ፡፡

**ደረጃ 4 የብድር ምክንያትን ማረጋገጥ**

መዝገብ ያዧ የጥሬ ገንዘብ መዝገቡንና የስብሰባውነ ቃለ ጉባኤ በማንበብ ባባለፈው ስበሰባ ስለ ተለቀቀው ብድር መረጃ ትሰጣለች፡፡ የስብሰባው መሪ የወሠዱትን ብድር መጠን አጠቃቀም ሁኔታ አባላቱን ትጠይቃለች፡፡ ማንኛውም አስፈላጊ መረጃ በቃለ ጉባኤው መዝገብ ውስጥ መሞላት አለበት፡፡

**ደረጃ 5 ደረሰኞች**

ሀ. አነድ አባል ገንዘቡን ይሰበስባል፡፡ በሚከተለው መሠረት መሠብሰብ አለበት

- ቅጣት
- ወለድ
- ዋናውን እንደገና በመክፈል
- ቁጠባ
- ሌሎች

ለ/ ምናልባት አንድ አባል መክፈል የነበረበት የብድር መጠን በስብሰባው ውስጥ መክፈል ሣይችል የቀረ እንደሆነ ለቡድኑ ስለሁኔታው መንገር አለበት፡፡ ውይይት ከተደረገበት በኃላ ቡድኑ የሚቀጥለው ቀን እና ምን ያክል መክፈል እንዳለበት ይወስናል፡፡

ሐ/ ምልባት ማንኛውም አባል በማንኛውም ምክንያት የወሰደችውን የብድር መጠን ሳትከፍል ብትቀር እና በዚህ ምክንያት ስብሰባ ላይ ሣትግኝ ብትቀር ቡድኑ ምክንያቷን በመለየት እና በሚቀጥለው ሣምንት ብድሯን መክፈሏን ለማረጋገጥ ያችን አባል ማነቃቃት አለበት፡፡

መ/ ምናልባት ማንኛውም አባል ስብሰባ ላይ ለመገኘት በማንኛውም ምክንያት ሣትችል ብትቀር እና ቁጠባ ለማደረግና የተወሰነ ብድሯን መጠን መክፈል ብትፈልግ በሌሎች አባለት በኩል መላክ ትችላለች፡፡ መጠኑ በስሟ ይመዘገባል ነገር ግን በስብባ መገኛ ማረጋገጫው ላይ ቀሪ ትደረጋለች፡፡ ሁሉም ደረሰኞች ከተገኙ በኃላ የሂሣብ መዝገቡ ከጥሬ ግንዘብ እና ከባንክ ደብተሩ ጋር ይስማማና ይኸው መረጃ ለአባላቱ ይሰጣል/ ይነገራል፡፡

ሠ/ ሌላ ማንኛዋም ክፍያ እንደ የአባላት የጉዞ አበል፣ የባንክ ወለድ፣ የመዝገብ ያዡ ክፍያና ወዘተ በተመሣሣይ ጊዜ ይፈፀማል

ረ. ጥሬ ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ ሣጥን ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

## ደረጃ 6 የብድር እቅድ ማዘጋጀት እና የማሠራጨት ሂደት

ሀ. ተወካዮች አባላት የብድር መጠናቸውን እንዲነግሯቸው ያደርጋሉ፡፡

ለ. ማንኛውም አይነት አዲስ የብድር እቅድ ከመመርመር በፊት ያ አባል ቀድሞ ወስዶ የነበረበውን ብድር ከነወለዱ በትክክል መመለሱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ሐ. አበሏ ቁጠባዋን በቋሚነትና በወቅቱ ማድረጓን በተጨማሪ ማረጋገጥ ያስፈልጋል

መ. መዝገብ ያዥ ለአባላቱ ስለመማልከቻ አቅራቢዋ የስብሰባ መገኘት ዝርዝር፣ ያቀረበችው የብድር እቅድ መጠን፣ የብድር ምክንያት እና የክፍያ ጊዜ ያሣውቃል

ሠ. አመልካቿ ለቡድኑ ስለብድር ክፍያ ጊዜ፣ በየምን ያክል ጊዜው እንደምትከፍል እና የብድሩ አይነት እና በምን አይነት ሃብቶች በኩል በድሯን ለመክፈል እንደሠባች ትገልፃለች።

ረ. ሁሉም አባላት በስምምነት የብድሩን መለቀቅ የመፍቀድ/ያለመፍቀድ ውሣኔ ይሰጣሉ እና የብድሩ መጠን ስንት እንደሆነም ይወስናሉ

ሰ. መዘገብ ያዡን የገንዘቡን እንቅስቃሴ ዝርዝር በጥሬ ገንዘብ መዝገቡ ላይ የራስ አገዝ ቡድን የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ላይ እና በአባሉ የአባልነብ ደብተር ላይ ይሞላል

ሸ. በእጅ ያለ ለብድር የሚሆን ገንዘብ እጥረት በሚኖርበት ጊዜ የራስ አገዝ ቡድን የአመልካቹን የብድር ጥያቄ መጠን ይቀንሣል።

## ደረጃ 7 የጥሬ ገንዘብ መዝገብ ማስማማት

ሀ. ሁሉምን ደረሰኞ እና ክፍያዎች ካጠናቀቀች በኂላ መዝገብ ያዥ ቀሪውን ጥሬ ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ መዝገብ እና በቡድን መመዝገቢያ ላይ ትፅፋልች። ይህ መጠን ከጥሬ ግንዘብ መዝገብ እና በስብሰባ ቃል ጉባኤ ላይ ከተፃፈው ጋር እንዲስማማ ይደረጋል።

ለ. ምናልባት ቀሪው የጥሬ ገንዘብ መጠን ከጥሬ ገንዘቡ መዝገቡ እና በሰብሰባ ቃለጉባኤው ላይ ከሰፈረው ጋር የማይስማማ ከሆነ በዚህ ጊዜ ሌላ አባል

ቀሪውን መጠን እንደገና መቁጥር አለበት፡፡ ምናልባት አሁንም መጠኑ የማይገጥም ከሆነ ከሁሉም አባላት ስምምነት መዝገብ ጠባቂዋ መጠኑን ለማስማማት ልዩነቱን እንደ ገቢ ወይም ወጪ ታደርጋለች፡፡መዝገብ ያዥዋ ማስታወሻ ታዘጋጅና የኘሬዝዳንቷን ፊርማ ታስፈረማለች

ሐ. ማንኛውም የተሞላ ነገር መሠረዝ የለበትም ገቢ የሆነ መጠን እና የተስተካከለው መጠን በጥሬ ገንዘብ መዝገብ ላይ እና በስብሰባ ቃለ ጉባኤው ላይ ሊቀየር ይችላል፡፡

መ. የጥሬ ገንዘብ ሣጥን መቆለፍ አለበት

**ደረጃ 8 ለብድር ተጠቃሚው ስለ ዋና ወለድ መጠን ማስታወሻ**

ሀ. መዝገብ ያዡ ስለ ዋናው ብድር መጠን ሁኔታ ያሣውቃል

ለ. የስብሰባው ተወካዮች ስለ ብድር ክፍያ ለአባላቱ ያስታውሣሉ፡፡ በተመሣሣይም ስለ ወለድ ክፍያ መጠን ማስታወሻ ይሰጣል

**ደረጃ 9 በስብሳ ላይ የመገኘት ማረጋገጫ እና ከስብሰባ ካለቀ በኂላ ማሰናበት ሁኔታ**

ሀ. ቡድኑ የትኛው አባል የጥሬ ገንዘቡን ሳጥን እንደሚያዝ እና የትኞቹ አባሎች ደግሞ ቁልፉን እንደሚይዙ ውሣኔ ያሣልፋል፡፡ በተመሣሣይ በሂሣብ ደብተሩ እና መዝገቡም ላይ ይወስናሉ፡፡

ለ. ማንኛውም አባል ወይም መዝገብ ያዥ በጥሬ ገንዘብ መዝገብ ላይ እና በስብሰባ ቃለ ጉባኤ ላይ በስብሰባው ላይ ስለመገኘታቸው ይሞላል እናም ሁሉም አባላት ፊርማቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ሐ. መዝገብ ጠባቂው ወደ ስብሰባ ዘግይተው የመጡ ሠዎችን ስም ያነባል እና ቅጣት በዚህ ስብሰባ ላይ ወይም በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ ይሰበሰባል፡፡

መ. የአባልነት ደብተሩን ለአባሉ መመለስ፡፡ መዝገብ ጠባቂው የተሞላውን የጥሬ ገንዘብ መዝገቡን እና የስብሰባ ቃለ ጉባኤውን መዝገብ በአባላት ፊት ያነባል፡፡

ሠ. መዝገብ ጠባቂውና ማንኛውም አባል በጥሬ ገንዘብ መዝገቡ ላይ እና በስብሰባው ቃሉ ጉባኤ መዘገብ ላይ ፊርማቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ረ. አንድ አባል ለጥምረቱ ወርሀዊ ሪፖርት እንዲደርስ ተመርጦ ያላካል

ሰ. ለሚቀጥለው ስብሰባ ቦታ መወሰን

ሸ. ተወካዩ ስብስባውን ታዘጋለች አናም ሁሉም አባላት ቁሣቁሣቸውን በጥንቃቄ ይዘው ይሄዳሉ

ቀ. ከስብሰባው በሚቀጥው ቀን ቁጠባው በባንክ ሂሣብ ቁጥር ውስጥ መቀመጥ አለበት እናም የማጠራቀሚያ ደረሰኝ በመዝገብ ይያዛል፡፡ በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ ለአባላቱ የማጠራቀሚያ ደረሰኝ እንዲያዩት ይደረጋል፡፡ ይህም ግልፅነትን በአባላት መካከል ለማስፈር ይረዳል

### የሣምንታዊ ስብሰባ ሂደት ማጠቃለያ

- በክብ መቀመጥ
- ፀሎት
- የስብሰባ መሪ መምረጥ
- የስብሰባ ተሣታፊዎች መዝገብ መያዝ
- አጀንዳ ማስቀመጥ
- የቀድሞውን ቃለ ጉባኤ መከለስ
- ሁሉም ከአጀንዳው ላይ ያሉ ጉዳዮችን ለውይይት መቅረባቸውን ማረጋገጥ
- ሁሉም አባላት በውሣኔ መስጠት ላይ መሣተፋቸውን ማረጋገጥ
- ከቁጠባ፣ ብድር ክፍያ እና ብድር አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የገንዘብ ዝዉውሩን ማጠናቀቅ
- በእያንዳንዱ ስብሰባ ጊዜ ቢያንስ ቢያንሰ አንድ ከብድርና ቁጠባ ውጭ የሆነ ጉዳይ ለውይይት ማቅረብ
- ቃለ ጉባኤውን ስብሰባው በሚካሄድበት ወቅት በመመዝገብ ለሁሉም አባላት ማንበብ
- ሁለም አባላት በዚህ መዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው

## 2.5 የቡድን አባል በሚሞትበት ጊዜ

በአባልነት ጊዜ እያንዳንዱ አባል አንድ ሰው መወከል አለበት፡፡ ሞት በሚመጣበት ጊዜ የዚያ ሰው ቁጠባ የወሰደው ብድር መጠን ተቀንሶ ቀሪው መጠን ሟች በሕይወት እያለ ለወከለው ሰው ይሰጣል፡፡

# ክፍል 2

## <u>የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት (CLA) ድርጅት መመሪያ</u>

# ምዕራፍ: 1 የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት መዋቅር  እና የአሠራር ዘዴዎች

## 1.1 የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ምን ማለት ነው

”የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት” የራስ አገዝ ቡድኖች በራስ አገዝ ቡድኖች ለራስ አገዝ ቡድኖች ዲሞክራሲያዊ አካል ነው፡፡ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ከ8-12 የሚደርሱ ቅርብ ለቅርብ ወይም በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሲሆን የሚሠራውም ራስ አገዝ ቡድኖች በትክክል በየግላቸው መስራት የማይችሉትን ስራ ነው፡፡ ይሁንና የራስ አገዝ ቡድኖችን ጥምረት የሚመሠርቱት የራስ አገዝ ቡድኖች ቁጥር እንደየሁኔታው ሊለያይ ይችላል››፡፡

የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በቀላሉ በአንድ አካባቢ ያሉ የብዙ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ማለት ነው፡፡ አያንዳንዱ አባል የራስ አገዝ ቡድን ቢያንስ በሁለት ተወካዮችን ወደ ጥምረቱ ይልካል፡፡ ሁሉም የራስ አገዝ ቡድኖች ጠንካራ ይሁኑ ወይም ጥራት ይኑራቸው አይኑራቸው እኩል ተወካዮችን ይልካሉ፡፡

**ቆምብሎ ማረጋገጥ**

‹‹የእድገት ደረጃን›› ለመለካት መስፈርቶችን ተቆጣጣሪዎቹ እኛ ነን

ካስቀመጡ በኃላ ከ8 የሚበልጥ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ከመመስረታቸው በፊት በዚህ ጊዜ የቡድኖች ደረጃ ያወጣሉ፡፡
የራስ አገዝ ቡድኖች ያሳለፉትን ወራቶች አትቁጠሩ (በጥራት ላይ የተመሰረቱ የራስ አገዝ ቡድኖች ከሆኑ ከ4-6 ወር በቂ ሊሆን ይሆናል)፡፡
ዝቅተኛውን አስፈላጊ መስፈርቶች የሚያሟሉት እና በአንድአካባቢ (1-2 ኪ.ሜ ሬዲየስ ) ውስጥ የሚገኙ የራስ አገዝ ቡድኖች የራሳቸውን ጥምረት መመስረት ይችላሉ፡፡




<u>የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ምስረታ</u>

**ደረጃዎች**

- የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አስፈላጊነት በተመለከተ በራስ አገዝ ቡድኖች መካከል ግንዛቤ መፍጠር
- በአንድ አካባቢ ያሉ የራስ አገዝ ቡድኖችን መመደብ
- በመሠረታዊ ስልጠናዎች ውስጥ ማለፍ
- ጠንካራ የራስ አገዝ ቡድኖችን መምረጥ
- የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ፅንሠ ሃሳብን ማስተዋወቅ

- የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላትን መምረጥ
- የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት መመስረት

1.2 በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ውስጥ ግብ ማስቀመጥ ራእይ መገንባት እንድ ጊዜ የራስ አገዝ ቡድን ጥምረት ከተመሰረተና ሚናውን ከተረዳ እያንዳንዱ አባል የራስ አገዝ ቡድን አሳታፊ የፈለጉት ዳሰሳ ያካሂዳሉ፡፡ ከፍላጎታቸው ውስጥ ዋና ዋና የሆኑ ሁለቱን ወይም አንዱን መርጠው ለራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ይልካሉ፡፡ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረቱ እነዚህን ፍላጎቶች ያጠናቅሩና በተጨማሪ ከፍላጎታቸው ውስጥ ዋና ዋናዎቹን በመምረጥ የመጀመሪያ የድርጊት መረሀ ግብራቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

የመነሻው እቅድ አጭር መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በቀላሉ ሊተገብሯቸው የሚችሉ ስራዎችን ማዘጋጀት አለበት፡፡

የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የመጀመሪያውን እቅዱን ለማዘጋጀት እና ተግባር ላይ ለማዋል ረጅም ጊዜ መውሰድ እንደሌለበት ይመከራል፡፡ የመጀመሪያ የተግባር እቅድ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ከተመሰረተ ከ3-4 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ዝግጁ መሆን አለባት፡፡ በዚህ ጊዜ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት መሠረታዊ ስልጠናዎችን ሲወስድ የራስ አገዝ ቡድኖች ደግሞ በዋና ዋና ፍላጎታቸው ላይ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡ ከተጠበቀው ጊዜ በላይ ተግባራዊ ማድረግ ከዘገየ ስራው እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡

አንድ ጊዜ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ከአንድ ወይም ሁለት ዙር በላይ የድርጊት ተግባር ውስጥ ካለፈ በኃላ አባላት በጣም ብዙ መተማመኛ ያገኛሉ፡፡ ከዚህ በኃላ የግብ ማስቀመጥ ልምድ ይኖራቸዋል፡፡ ግቦች የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ ሊሆን ይችላሉ፡፡ የአጭር ጊዜ ግቦች የሚባሉት በአንድ አመት ውስጥ ሊደረስባቸው የታቀዱ ሲሆኑ የረጅም ጊዜ ግብ የሚባሉት ደግሞ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊደረስባቸው የሚታቀድ ማለት ነው፡፡

<u>ራዕይን ማዘጋጀት</u>

የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ራዕይ በሚኖርበት መህበረሰብ ውስጥ ጥሩ ለውጥ ወይም ተፅዕኖ መፍጠር ነው፡፡

<u>የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የራዕይ ምሳሌ</u>

የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በጣም ጥሩ ቀጣይነት ያለው ጥሩ ለውጥ በማህበረሰቡ ውስጥ በፖለቲካ ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ባጠቃላይ የራስ አገዝ ቡድን አባላት ደግሞ በተለይ እንዲያመጡ ያነሣሣል፡፡

## ተልዕኮን ማዘጋጀት

የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተልዕኮ የፌደሬሽኑ አጠቃላይ  የተመሰረተበት ምክንያት አላማ ሠፊ ሀተታ ነው፡፡ የተልእኮው ሀተታ ድርጅቱ እንዴት የተሻለ ማህበረሰብን ለመፍጠር አስተዋፅኦ ከሚያደርገው ራዕይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ተልእኮ ሀተታዎች ለእያንዳንዱ የራስ አገዝ ቡድን ጥምረት /ፌደሬሽን የተለየ እና የራሱን ተልእኮ ለመግለፅ የሚያነቃቃ ነው፡፡

### የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የተልእኮ ምሳሌ

በራስ አገዝ ቡድኖች የተግባር እና ግለሰቦች ራሳቸውን እንዲረዱ በማብቃት የሴቶች እና የሠፊውን ማህበረሰብ በጠቅላላ የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊ እና የፖለቲካ ሁኔታዎችን በጥሩ ሁኔታና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማሻሻል፡፡

## ስነ ምግባር መርህ ማዘጋጀት

ስነ ምግባር ማለት የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባለት አጋሮቻቸው የድርጅታቸውን አላማ ሲያስፈፅሙ የሚመሩበት መርሆች ወይም እምነቶች ናቸው፡፡

## የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የስነ ምግባር ምሣሌዎች

**ራስን መርዳት፡-** እያንዳንዱ የራስ አገዝ ቡድን አባላት በራሱ/ሷ ጥረት ራሱን/ራሷን ህይወት መቀየር አለባት፡፡

**ትብብር፡-** በሁሉም ተግባሮቻችን ላይ እንደ መሪ ደረጃውን የጠበቀ እሣቤ እኛ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ጠንክረን እንተባበራለን፡፡

**ተግባቦት፡-** በአባላት መካከል ታማኝነት ፣ ጥሩ ስነምግባር ፣ የቡድን ስራ ባሕል እና እርስ በርስ መረዳዳት እንዲኖር ድጋፍ እናደርጋለን፡፡

**ተነሳሽነት፡-** በአባላት መካከል የግለሠቦችን እና የቡድኖችን አዳዲስ ነገሮች መፍጠርን መነሳሳትን እናበረታታለን እንሸልማለን፡፡

## <u>የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ግቦች ማዘጋጀት</u>

## <u>የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የተልእኮ ሀተታ</u>

የተልዕኮ ሀተታ የራስ አገዝ ቡድኖችን አጠቃላይ አቅጣጫ ሲገልፅ ግቦች ግን በጣም ውስጥ ናቸው፡፡ ግቦች ማለት የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተልእኮውን ለማሳካት የሚያስገኛቸው ውጤቶች ናቸው፡፡

ግቦች በቁጥር የተወሠኑ እና ልዩ በሆነ በድርጅቱ ተልእኮ ላይ ያነጣጠሩ አጠቃላይ ሀተታዎች ናቸው፡፡ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ግቦች በማህበረሰብ ተግባርና በህብረተሰቡ ተግባር ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡

ከማህበረሰብ ተግባር ጋር የተያያዙ ግቦች እነዚህ ማንኛውን አይነት ለአንድ መንደር ማህበረሰብ ጥቅም የሚተባበሩ ተግባሮች ናቸው፡፡ ይህም የህዝብን አገልግሎቶች እና ሌሎች ጉዳዮችን ለመጠገን ፣ ለመፍጠርና ለማስገኘት ይረዳሉ፡፡

ምሳሌ፡ የንፁህ ውሃ ፕሮጀክት

የመንገድ ጥገና ወ.ዘ.ተ

**ከማህበራዊ ተግባራት ጋር የተያያዙ ግቦች፡-** እነዚህ ማንኛውም የግለሰብን ወይም የማህበረሰብ እጥረት ወይም ተጋላጭነት ለማጥፋት የሚተገበሩ ተግባራት ናቸው፡፡

ምሳሌ፡ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን የማስቀረት ጥረት

- የቤት ውስጥ ጥቃትን መታገል ወ.ዘ.ተ

## 1.3 <u>የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት መወቅር</u>

የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ውሳኔ ሰጭ አካል ከ16-40 አባላት የሚይዝው ጠቅላላ ጉባኤ ነው ሁሉም የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት (የድርጅቱን መዋቅር ተመልከት)። ጠቅላላ ጉባኤው የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የቢሮ ሰዎች በዲሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ይመርጣል።

- ከ8-12 የራስ አገዝ ቡድኖች (በተለየ ምክንያት ብቻ ከ8 በታች ሊሆኑ ይችላሉ) ስድስተኛ ወራቸውን ያጠናቀቁ እና በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ከሆነ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ማቋቋም ይችላሉ።
- ከያንዳንዱ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሁለት ሁለት ተወካዮች በራስ አገዝ ቡድኑ ጥምረት ውስጥ ይወከላሉ።
- የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት መዝገብ ፀሐፊ እና ሁለት ተወካዮች በስምምነት ከራስ አገዝ ቡድኖች መካከል ተመርጠው በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ውስጥ ይወከላሉ።
- የራስ አገዝ ቡድን ጥምረት ተወካዮችና መዝገብ ፀሐፊ ከተለያየ ቦ□ እንዲሆኑ ይመከራል።
- የራስ አገዝ ቡድኑ ጥምረት ፍላጎት መሰረት የንኡስ ኮሚቴው ቁጥር እና ተግባር ይወሰናል።
- የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተግባሮቻቸውን በጥሩ ሁኔ□ ለመ□□ ንዑስ ኮሚቴዎቻችን ያቋቁማሉ። ንዑስ ኮሚቴዎቹም በራስ አገዙ ቡድኖች ጥምረት የተቀመጡትን የተግባር እቅዶችና ግቦች ይፈፅማሉ። በእያንዳንዱ ንዕስ ኮሚቴ ውስጥ በተለምዶ ከ4-6 የሚሆን አባላት አሉ። የንዑስ ኮሚቴ አባላት ከራስ አገዝ ቡድን ጥምረት ይመረጣሉ ነገር ግን ዓቂቶች እንደችሎታቸው መሰረት ከአባል የራስ አገዝ ቡድኖች ውስጥ ሊመረጥ ይችላሉ።




## 1.4 የራስ አገዝ ቡድን ጥምረቶች አስፈላጊነት እና ሚና

በፅልን □ንደተቀመጠው የስራ አገዝ ቡድኖች ጥምረት

- ❖ ከራስ አገዝ ቢድኖች ተግባር ጋር የማይጋጭ በግልፅ የተቀመጡ ተግባሮች አሉት
- ❖ □ፅል ዓቅም በሚ□ስፉኙ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ አይገባም ለራስ አጋዝ ቡድኖች የመረጃ ፣የሀብት፣ የአቅርቦት ትስስር ያመቻቻል እንጂ

ም□ም ፅልን ለመሆን የራስ አገዝ ቢድኖች ጥምረት 6 ዋና ዋና ተግባር አሉት እነሱም፡-

1. የራስ አገዝ ቡድኖችን ማጠናከርና አዳዲሶችን መፍጠር
   - አባል የራስ አገዝ ቡድኖችን መንከባከብ መከታተል ስልጠና መስጠትና ሂሳብ መመርመር
   - የራስ አገዝ ቡድኖች የውስጥ አለመግባባታቸውን በራሳቸው መፍታት ሲ□ቅታቸው የእነዚህ እራስ አገዝ ቡድኖች □ለመፅባባታቸውን መአ ታት፡፡

- አላ□ቱ በተቆኘ ቷ□ በአካባቢው አዳዲስ የራስ አገዝ ቡድኖችን ማቋቋም

2. ከሌሎች አገልግሎት ወጭዎች ጋር ትስስር በመፍጠር የሀብት ማሰባሰብ
   - የቁሳቁስ ሀብትና የማህበራዊ አገልግሎት ለማግኘት የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ትስስር እንዲፈጥር ይበረታታል፡፡
   - የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ስራዎቻቸውን ለመደግፍና የተወሰኑት የአስተዳደር ወጭዎችን ለመሸፈን ፈንድ ማሰባሰብ □ስ□ልፉል፡

3. በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ኘሮጀክቶችን ማቀድና መተግበር
   - ፍላጎቶችን ከመዳሰስ ባለፈ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት (CLA) ለአባሎቻቸውና አጠቃላይ ለማህበረሰባቸው የሚተገብሯቸው ብዙ በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ኘሮጀክቶች ሊኖሩ ይችልሉ፡፡ የራስ አገዝ ቡትኖች ጥምረት አሳታፊ የሆነ የለፍላጎት ትነትና ተግባርና ፍላጎቶችን በ□ረ□ □ማስቀመዓ ስራ ያከናውናል፡፡ ከሁሉም አንገብጋቢ የሆኑ ኘሮጀክቶች በቅድሚያ ይተገበራሉ፡፡ እዚጋ እንደገና የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ኘሮጀክቶችን ለመተግበር ያስችለው ዘንድ ከእርዳት ሰጪዎች እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪ አካላት ሀብት ያ□ላልፉሉ፡፡ አንዳንድ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የሚያነሷቸውና የሚተገብሯቸው ምሳሌ ኘሮጀክቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

     - ለትንንሽ ህፃናት ቅድመ ትምህርት ቤት መዋያ
     - ትምህርት ለሚማሩ ህፃናት የጥናት ክፍሎች
     - መሀይምነትን ለማስወገድ ትምህርት ለራስ አገዝ ቡድኖች አባላት እና ለሌሎች
     - □□ህል ወአ□
     - □እህል መጋዘን በመከር ወቅት እህል ገዝቶ በማቆየት መሸጥ
     - □ተፋሰስ ልማቶች

4. ማህበራዊ ችግሮችን መአ ታት

- ልማት በማህበረሰብ ውስጥ የስነምግባር ዘዴ ለማቋቋም መብትን የማስከበር እና የስራ ሀላፊነትን በወንዶች በሴቶች በልጃገረዶች እና በወንድ ልጆች ለማግኘት ያለመና በተመሳሳይ በነዚህ መካከል ግንኙነት እንዲጠናከርና እንደገና እንዲጀመር ይረዳል።
- የራስ አገዝ ብድኖች በውይይታቸው ቁ□ ማህበራዊ ጉዳዮችን ያነሳሉ። ወዲያዉኑም በትክክለኛ እና በተሳሳቱ ስነ ምግባሮች እና በጠቃሚ በ□ጂ የማህበራዊ ልምዶችና ተግባሮች ላይ ከስምምነት ጁ□ርሳሉ። ይህንን መቀየር መጥፎ ስራዎችን ለረጅም ጊዜ ይዞ የቆመ ጉልበት ያለው ሀይል ስላላ ቀላል አይሆንም ለምሳሌ፡-
    - የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ እንዲቆም መቀስቀስ
    - □ቤት ውስጥ ጥቃትን መ□ቆል ወ□ተ...

5. የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አስተዳደራዊ ተግባር
    - የማህበራዊ አመቻቾች ለራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሪፖርት ማትረፅ ጁ□ምራሉ
    - የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ለአስተዳደሪዊ ወጪ አላ□ታቸው ገንዘብ ይሰበስባሉ።
        - ከራስ አገዝ ቡድኖች አስተዋፅኦ
        - ተግባራዊ ከሚደረጉ ኘሮጀክቶች የአስተዳደር ወጪ
        - ለራስ አገዝ ቡድኖች ከሚሰጥ አገልግሎት የአገልግሎት □አ□
        - ከከአተኛ ኢንቨስትመንት /በራስ አገዝ ቡድኖች ከሚተዳደር □ቅተኛ አደጋ ካለው የገቢ ማስገኛ
    - የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ለማህበራዊ አመቻቾች ሊያቀያቸው ከፈለጉ የኪስ ገንዘብ መክፈል ይጀምራሉ።

6. ትስስር እና ግንኙነት መፍጠር
    - በማህበራዊ ፣በሚኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ጥሩ ሰኝ እድገት እና ስፋ ያለ ውጤት ለማስገኘት የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ትስስር እና ግንኙነት ከተለያዩ አካላት ጋር መመስረት አለበት።

- የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ከተለያዩ ኤጀንሲዎች መንግስት በአንድ አይነት ስራ ላይ ያሉ ክፍሎችን የማህበረሰብ አደረጃጀት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ወዘተ ጨምሮ ግንኙነታቸውን ማሳደግ አለባቸው።

# ምክራአ 2

# የውስጥ የስራና የተግባር መመሪያ

2.6 □ዉ፡ስዓ ስራቸውን በዘዴ ለማከናወን የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት መመሪያዎችን በስምምነት ማዘጋጀት አለባቸው መመሪያዎች ሁሉም አባላት ሊከተሉዋቸው የሚችሉና የራስ አገዝ ቡድኖችን አላማ ለማሳንካት ድጋፍ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው።

2.7 የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት ለጥምረቱ ቀላል መመሪያዎች እንዲያዘጋጁ ነገሮች ይመቻቹላቸዋል። እነዚህን መመሪያዎች ከፃፉ በኃላ እንደህጋቸው በመውሰድ በነሱ መሰረት ስራቸውን ያከናውናሉ። አባላት የራሳቸውን መመሪያዎች እና ህጎች አዘጋጅተው በቃለ ጉባኤ መዝገባቸው የመጀመሪያ ገፅ ላይ ይመዘገወቧቸዋል። መመሪያዎቹ በጣም መሰረታዊ ናቸው። ወ□ ስብሰባ በቋሚነት ስለመምጣት፣ ወደ ስብሰባ በትክክለኛው ሰዓት ስለምጣት፣ በቋሚነት ስለ መቆጠብ እና እንዱ ሌላዉ፡ ማ□በር እንዳለባቸው ሊያወሩ ይችላሉ።

2.7.1 **ከስብሰባ ጋር የተያያዙ መመሪያዎች** የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ወርሀዊ ስብሰባ የግድ መደረግ አለበት። □ተለ□ ስብሰባ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊጠራ ይችላል። የስበሰባ ቀን፣ ሰ□ት (በወር ውስጥ የተወሰነ ቀን ቢሆን ይመረጣል) እና ቦታ በአባላት ስምምነት እና የቻለውን ያክል ብዙ ሰው ሊገኝበት የሚችል ቀን መወሰን አለበት።

2.7.2 በስብሰባ መቶኛት ማረጋገጥ በተያያዘ መመሪያዎች የሁሉም የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት በስብሰባው ላይ መገኘ ት የግድ ነው። ምናልባት ማንኛውም አባል በስብሰባው ላይ

መቆናት የማይችል ከሆነ ምክንያቱን ቀደም ብሎ በመናገር ማሳወቅ አለበት፡፡ ምናልባት የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባል ቀደም ብለው መረጃ ሳይሰጡ ከስብሰባ ቢቀሩ ወጁም አርፍደው ቢመጡ ከነዚህ የራሰ አገዝ ቡድኖች ላይ ቅጣት ጁጣላል፡፡ ለቅጣት የሚሆነውን መጠን ቡድኑ ይወስናል፡፡ የቅጣቱ መጠን የተጋነነ መሆን የለበትም በዚህ የተነሳ ሁሉም የራስ አገዝ ቡድኖች አባላት ሊከፍሉ ይችላሉ በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ስብሰባ ላይ ቢያንስ 80 በመቶ የሚሆኑ አባላት መገኘት አለባቸው፡፡

2.7.3 **ከራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተወካዮች የስራ ጊዜ ጋር የተያዙ *መመሪያዎች*** የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተወካዮች የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡ ምናልባት አንድ ሰው ሀላፊነቱን ሙሉ በሙሉ መወጣት ሳይችል ቢቀር በጠቅላላ ጉባዔው ስምምነት ያ ሰዉ □ስራ ጊዜው ሳይጠናቀቅ ከተወካይነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡

2.7.4 **ከውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዙ *መመሪያዎች*** ሁሉም አይነት ውሳኔዎች በራስ አገዝ ቡድኖችን ጥምረት ውስጥ በሁሉም የስራ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት ስምምነት ይፈፀማል፡፡ በማንኛዉም ቶቴጁ ላጁ ዉሳኔ ለማሳለፍ 80 በመቶ የሚሆኑ አባላት መገኘት □ፅት ጁላል፡፡

2.7.5 ከአባል የራስ አገዝ ቡድኖች ጋር ከተወያዩ እና በስብሰባቸው ይህን ተከታትለው ውሳኔ ካባለፉ በኋላ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ማንኛ ውም አይነት ሚና እና ህግ ያቅዳል፡፡

2.7.6 የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በአባል በራስ አገዝ ቡድኖች አስተዳደራዊ እና የአስተዳደር መመሪያዎች ጣልቃ አይገበቡም እናም □□ራስ አገዝ ቡድኖች አባል ነፃነት ያከብራሉ፡፡

2.7.7 የአስተዳደራዊ ወጭዎቹን እንዲሸፍንበት አባል የራስ አገዝ ቡድኖች ለራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በየወሩ ጥቂት አስተዋፅኦችን ይከፍላሉ፡፡ የሚከፈለው መጠን በራስ አገዝ ቡድኖች እና በራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምር ስምምነት መሰረት ይሆናል፡፡ በተቻለው ጊዜ የራስ አገዝ ቡድኖችን ጥምረት አስተዳደራዊ ወጭዎችን የሚሸፍንበትን ገንዘብ ጥሩ ቦ□ ለማስቀመጥ በስማቸው የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፡፡

**2.7.8** ከራስ አገዝ ቡድኖች ተመሳሳይ ባልሆነ መልኩ በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት ውስጥ ምንም አይነት የብድርና የቁ□ባ ተፅባር አልፈፀመም:: የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት በተመሳሳይም የራስ አገዝ ቡድኖች አባላት ስለሆኑ ምንም አይነት በግል የኢኮኖሚ ዓቅም በጥምረቱ ዉስዓ ማፅኘት የለባቸውም:: ዋና ጥቅማቸው ከማህበረሰቡ □ዉቅና ማፅኘት ነው:: አንድ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በምንም አይነት የቀን ከቀን የንግድ ስራ ዉስዓ አይንቀሳቀስም:: ይሁንና ለራስ አገዝ ቡድኖች የንግድ አጋጣሚ ማመቻቸት ግን ይችላል::

| | |
|---|---|
| የራስ አገዝ ቡድኖች 15-20 ሴቶች | የመጀመሪያ አባልነት አጠቃላይ አካል<br>• ቁጠባዎች/ብድርና ሁሉም የኢኮኖሚ ተግባር<br>• በአባላት መካከል ፍቅር<br>• መሰረታዊ ማህበራዊ ጉዳዮች በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ውስጥ |
| የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት<br>(8-12 የራስ አገዝ ቡድኖች) | የውክልና ደረጃ<br>• የራስ አገዝ ቡድኖች ማጠናከር እና አዳዲሶችን መመስረት<br>• ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር<br>• በማህበረሰቡ ውስጥ ስነምግባር □□ መአ□ር |
| ፌዴሬሽን (8-12 የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት) | የተቋሙ ምንነት<br>• የተቋሙን ማንነት ለማቆየት/ለመያዝ<br>• ለህዝቡ ጠቃሚ ለሆኑ ፖሊሲዎች መቀስቀስ እና መጎትጎት<br>• ከውጭ አካላት ጋር መስተጋብር ለመፍጠር ህጋዊ አካል |

# ክፍል 3

# በፌደሬሽን ደረጃ የድርጅት መመሪያ

### 3. በፌደሬሽን ደረጃ

ፌደረሽን የማህበረሰብ ተቋም ከፍተኛው አካል ነው። ፌዴሬሽን በሚቋቋምበት ደረጃ እያንዳንዳቸው ከ8-10 የሚሆኑ የራስ አገዝ ቡድኖች አሏቸው። ከ8-10 በሚሆኑ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ይዋቀራሉ። ይህም ማለት ወደ 200 የሚደርሱ ቤተሰቦችን ይወክላል ማለት ነው። አንድ ቤተሰብ በአማካኝ አምስት አባላት ይኖሩታል ተብሎ ቢታሰብ አንድ ፌደሬሽን 10,000 የሚሆኑ ሠዎችን በቀጥታ ተፅእኖ ማድረግ ይችላል ማለት ነው። ይህ የማህበረሰብ ኃይል ነው። ብዙ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በአመታት ውስጥ እየተመሠረቱ በሄዱ ቁጥር የፌደሬሽኑ አቅም ማደጉ ይቀጥላል።

ምንም እንኳን ፌደሬሽን ከፍተኛው የማህበረሰብ አካል ቢባልም ይህ ማለት ግን የራሰ አገዝ ጥምረት የሚወክሉት የፌደሬሽን አባላት እና የራስ አገዝ ቡድኖች አባላት በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ውሰጥ የተወከሉት ፍፁም የሆነ ስልጣን አንዳላቸው ያሣያል ማለት አይደለም። ሀይሉ አጠቃላይ አሁንም ያለው በራሰ አገዝ ቡድኖች በተወከለው አካል እጅ ነው። የራስ አገዝ ቡድኖች አባላት የማህበረሰብ ተቋም "ባለቤቶች" ሲሆኑ ዋናውን ውሣኔ የሚያሣልፉትም እነሱ ናቸው። የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ፌደሬሽን ለተወሰነ በሰርአቱ ለተለገፀ ተግባር የተቀመጡ የራሰ አገዝ ቡድኖች አባላት ተወካዮች ናቸው።

## 3.1 የፌደሬሽን ባሕርያት

**የመህበረሰብ ተቋም በፌደሬሽን ደረጃ የሚከተሉት ባሕርያት ሊኖሩት ይችላሉ**

- በተግባሩ ላይ መሠረት በማድረግ በግልጽ የተለየ ባሕርያት አሉት
- ፌደሬሽን ከራስ አገዝ ቡድኖች እና ከራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ጋር የሚስማማ የራሱ የሆነ አላማና ተግባራት አሉት
- የፈደሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የፈደሬሽኑን ስራዎች ያቅዳል ይተገብራል።

3.1.1 ፌደሬሽን በራሱ መብቶችና የተለየ ማንነት ያለው ተቋም ነው። የፈደሬሽን ማንነት በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረትና በራስ አገዝ ቡድኖች ውስጥ ካሉ አባሉቱ ራእይና ተልእኮዎች ይመነጫል።

3.1.2 የፌደሬሽን ተወካዮች አካል ከአባል የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሁለት ሁለት ተወካዮች የተወጣጣ ነው፡፡ ተወካዮችም በራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በተዘጋጀ መስፈርት መሠረት ባደርገ ምርጫ በጥንቃቄ ይመረጣሉ፡፡ የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተወካዮች ስምምነት ለተደረሰበት ጊዜ ያክል በፌደሬሽኑ ውሰጥ ያገለግላሉ፡፡ ይህ ጊዜም 3 አመት ነው፡፡ የአንድ አባል ውክልና በራስ አገዝ ቡድን ውስጥ ያለው ውክልና ግን ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሁንና አባሉ በራስ አገዝ ቡድኑ ውስጥ አባል ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን አባሉ የራስ አገዝ ቡድን አባል ካልሆነ እሱ ወይም እሷ ከዚህ በኋላ የፌደሬሽን አባል ሆነው መቀጠል ግን አይችሉም፡፡ ተወካዮች መቀየር በአንድ ጊዜ የሚፈፀም አይደለም፡፡ የፌደሬሽኑ አባላት በሁለት ወር አንድ ጊዜ ይገናኛሉ፡፡ በመጀመሪያ ፌደሬሽኑ በተቋቋመበት ጊዜ ግን በተደጋጋሚ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡

3.1.3 ፌደሬሽን የማህበረሰብ ሕጋዊ አካል ሲሆን በሚመለከተው ለፌደሬሽኑ አሠራር ባህርይ ቅርበት ባለው የመንግስት ኤጀንሲ የተመዘገበ ነው፡፡ ይህም ሕጋዊ መአቀፍ በድንብ ከተጠና በኋላና በራስ አገዝ ቡድኖች ፀንሰ ሃሣብ ጋር ያለው ግንኙነት ከተመረመረ በኋላ ይፈፀማል፡፡ ምናልባት ምንም አይነት የሕግ ማአቀፍ ከዚህ ሃሣብ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ አዲስ ሕግ እንዲዘጋጅ መጐትጐት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የፌደሬሽኑ ሕግም ከሁሉም የሀገሪቱ ሕግ ጋር መጣጣም አለበት፡፡

3.1.4 ፌዴረሽኑ የፌደሬሽኑን ተወካዮች ወክሎ የሚሰራ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አለው፡፡ የፌደሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚዎች ፌደሬሽኑ በሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች መሠረት ከፌደሬሽኑ አባላት ውስጥ ይመረጣሉ፡፡ የፌደሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ኮሜቴዎች ለተወሰነ ጊዜ ያገለግላሉ፡፡ አንድ አባል የፌደሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊሆን የሚችለው እሱ ወይም እሷ በፌደሬሽኑ ውስጥ እስካሉ ድረስ ነው፡፡ የፌደሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስራውን በደንብ ያከናውን ዘንድ አባላቱ ከ8 መብለጥ የለባቸውም፡፡

3.1.5 በአጠቃላይ ጉባኤው ተሣትፎ በዳበረና ሁሉም በሚጋሩት ሁኔታ ፌደሬሽኑ ግልጽ የሆነ ራእይ፣ ተልእኮና አላማ ያዘጋጃል፡፡

3.1.6 ፌደሬሽኑ በራሱ የለያቸውን ስራዎች ለማከናወን ስራን መሠረት ያደረጉ ኮሚቴዎችን ያዋቅራል፡፡ ይህ ኮሚቴ ለተወሰነ ጊዜ ያገለግላል፡፡ ፌደሬሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜና ሁኔታ ባለሞያዎችን ሊቀይር ይችላል፡፡ እነዚህ የውጭ ባለሞያዎች ስራን መሠረት አድርጉ በተቋቋው ኮሚቴ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ፌደሬሽኑ የሠው ኃይል ለሚያስፈልጋቸው ስራዎች ቋሚ ሠራተኛ ሊቀጥር ይችላል፡፡

3.1.7 ፌደረሽኖቹ ለአባላት አስፈላጊ የሆነ እውቀትና መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንድ ፌደሬሽኖች ለዚህ አላማ የተቋቋሙ የመረጃ መአካላት አሏቸው፡፡

3.1.8 ፌደሬሽኑን የራሱ ቢሮ፣ የመገናኛ መሣሪያ እና የታተሙ የፅሕፈት መሣሪያዎች ይኖሩታል፡፡

## 3.2 የፌደሬሽን ምስረታና ስራ መጀመር

- ፌደሬሽን ሊመሠረት የሚችለው የማህበረሰቡ ተቋም በብዛትና በጥራት ትክክለኛ እድገት ላይ በሚደርስበት ጊዜ ነው፡፡
- የፌደሬሽኑ አቅም የመሀበረሰብ ተቋሙን እንዲያስተዳድር ከተገነባ በኋላ ድጋፍ ከሚያደርጉ ድርጅቶች ኃላነቱን ይቀበላል፡፡

3.2.1 ፌደሬሽን ሊመሠረት የሚችለው ጊዜው ሲደርስ ነው፡፡ የቁጥር አመላካች የሚሆነውም በቂ የሆኑ የራሰ አገዝ ቡድኖች መኖርና ከ8-10 የሚሆኑ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሲኖሩ ነው፡፡ ጥራትን በተመለከተ ደግሞ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ጠንካራና ተግባራቸውን እና ኃላፊነታቸውን በጥሩ ሁኔታ መወጣት የሚችሉ ሲሆኑ ነው፡፡ የፌደሬሽን ምስረታውን ማጓተትና ኃላፊነትን በወቅቱ ያለማስተላለፍ የማብቃቱን ሂደት ያቀጭጨዋል፡፡

3.3.2 ከላይ የተጠቀሱት አመላካቾች /ክፍል 4.8 ተመልከት/በራስ አገዝ ቡድኖቹ ጥምረት መካከል ውይይት ሚደረግባቸውን ስምምነት ላይ ሲደርስ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች አዲሱን ፌደሬሽን ለመመስረት ሂደቱን ማሣለጥ ይጀምራሉ፡፡

3.2.3 የፌደሬሽን ፅንሰ ሃሣብ የራስ አገዝ ቡድኖችን ለራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት አባላት ይብራራላቸዋል፡፡ አንድ ጊዜ ከሆኑና ስምምነታቸውን ካሣወቁ የደሠሣው ሂደት ይጀመራል፡፡ ደሠሣውም በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረቶች እና በኘሮጀክት ኦፊሰሩ/በመሀበረሰብ አመቻች በጋራ በተመረጡ ቁልፍ አመላካቾችን መሠረት በማድረግ ይፈፀማል፡፡ ዳሠሣ የተደገባቸው እና ጥሩ ጥራት ያላቸው ሆነው የተገኙት የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረቶች የፌደሬሽን አባል ይሆናሉ፡፡

3.2.4 በእያንዳንዱ የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በጥንቃቄ ሁለት አባላት ይመረጡና በዙር እየተቀያየሩ በፌደሬሽኑ ውሰጥ የራስ አገዝ ቡድናቸውን ጥምረት ይወክላሉ፡፡ መስፈርቱ ሊለያይ ይችላል፡፡ የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በፌደሬሽኑ ውሰጥ ያለው የውክልና ጊዜ 3 አመት ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ አንደኛው ተወካይ በአንድ አመት ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያል በዚህ ሁኔታ የአባላት መተካካት በአንድ ጊዜ ሣይፈፀም እንዲቆይ ይሆናል፡፡

3.2.5 የኃላፊነት ማስተላለፍ ልምምድ ቀድሞ ድጋፍ በሚሰጠው ድርጅት ይሠሩ የነበሩትን ስራዎችና ፌደሬሽኑ በራሱ ተረክቦ ተግባራዊ እንደያደርጋቸው የሚፈልጉትን የቀሩ ተግባራት መለየት ይደረጋል፡፡ በዚህ ልምምድ በድጋፍ ሰጪ ድርጅቱ እስካሁን የሚሠሩ ተግባራት ይዘረዘራሉ፡፡በፌደሬሽኑ ጥልቅ እይታ ከተደረገባቸው በኂላ ፌደሬሽኑ እነዚህን ተግባራት እንዲረከብ ከተግባራቱ ጋር ይፃፋል የጊዜ ገደቡ ምናልባትም ዙር ባለው ሁኔታ ሊሆን ይችላል፡፡

3.2.6 በኃላፊነት ማስተላለፍ ልምምድ ወቅት የአቅም ግንባታ ፍላጐቶች ይለያሉ፡፡ እቅድ ይወጣና ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የውጭ አሠልጣኞች ጋር ውል ሊገባ ይችላል፡፡

3.2.7 አንድ ጊዜ ፌደሬሽኑ ተግባራቱን ለመረከብ መተማማን ደረጃ ላይ ከደረሰ ረጅ ድርጅት ስራውን ያቆማል፡፡ ይህ በረጅ ድርጅቱ የተወሰደ እርምጃ የማህበረሰቡን ተቋም መብቃት በመቀበል በፍላጐት ያደረገው ነው፡፡ ፌደሬሽኑ የረጂ ድርጅቱን በስራ ላይ ያሉ ቋሚ ንብረቶችም ሊረከብም ይችላል፡፡

## 3.3 የፌደሬሽን ተግባራት

ፌደሬሽኑ በተግባራቱ ላይ መሠረት ያደርጉ የታወቁ ባሕርያት አሉት

- ፊደሬሽኑ ከራስ አገዝ ቡድኖች እና ከራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ጋር የሚስማማ የራሱ የሆነ አላማዎችና ተግባራት አሉት፡፡
- የፌደሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የፊደሬሽኑን ተግባራት ያቅዳል ይተገብራል፡፡

3.3.1 በአዲስ የተመሠረተ ፌደሬሽን ራእዩን፣ ተልእኮውን እና ግቡን ለማዘጋጀት በስልታዊ እቅድ ማዘጋጀት ሂደት ውሰጥ ያልፋል፡፡ ይህ የሁሉም መሀበረሰብ የሚጋሩት የጋራ አመለካከት ስለሚሆን በሂደቱ ውስጥ የራስ አገዝ ቡድኖችና የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ተወካዮች ይሣተፋሉ፡፡ ነፃ ሆኖ ለመስራት ይህንን ተግባር የረጅ ድርጅቱ ሰው ከሚያሣልጠው ይልቅ ከውጭ የመጣ ሰው ቢያሣልጠው ጥሩ ይሆናል፡፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የራሣቸው ትኩረት የሚሰጡባቸው ሁኔታዎች ስላሉ ሣያውቁት በፌደሬሽኑ ስልታዊ እቅድ ላይ ተፅእኖ ሊያሣድሩ ይችላሉ፡፡

3.3.2 ፌደሬሽኑ ከረጅ ድርጅት ላይ የመሃበረሰቡን ተቋም አስተዳደራዊና የአመራር ኃላፊነት ይረከባል፡፡ በፊደሬሽኑና በረጅ ድርጅቱ መካከል የኃላፊነት መተላለፍ ልምምድ ይካሄዳል፡፡ ስለሆነም ፊደሬሽኑ ቀስ በቀስ እስከ አሁን በረጅ ድርጅቱ የሚሠሩ ስራዎችን ይረከባል ማለት ነው፡፡

3.3.3 ለራሰ አገዝ ቡድኖች ለራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ኃላፊነትን በመወከል ፊደሬሽኑ የመሀበረሰብ ተቋሙ በጥሩ ሁኔታ እየሠራና በዲሞክራሲያዊ መርህ እየተዳደረ እንዳል ያረጋግጣል፡፡

3.3.4 ፊደሬሽኑ ለመሃበረሰብ ተቋሙ ሕጋዊ ግንኙነት ይሰጣል፡፡ ይህም ስለሆነ ፊደሬሽኑ የተለያዩ አማራጮችን እና በሀገሪቱ ውሰጥ ካለው ሕጋዊ ባለስልጣን ይመዘገባል፡፡ ከዚህ ጋር የሚገናኙ ሕጐች ባማይኖሩበት ሁኔታ ፊደሬሽኑ ምቹ የሆነ ሕግ እንዲወጣና ሕጋዊ ማንነት እንዲያገኙ መጐትጐት አለበት፡፡

3.3.5 ፈደሬሽኑ መሀበረሰብ እኩልነት፣ ሠላም እና ፍትህ እንዲያገኝ አልግሎት ይሰጣል። በማሃበረሰብ ውሰጥ መብታቸው የተጣሱ አባላት ወደ ፌደረሽኑ ቢሮ ሊመጡ ይችላሉ።

3.3.6 ፈደሬሽኑ አጠቃላይ አባሉቱና መሀበረሰብ አስፈላጊ ስለሆኑ ጉዳዮች እውቀትና መረጃ ማገኘታቸውን ያረጋግጣል። ይህ ምናልባት የመረጃ ማአከል በማቋቋም ሊሆን ይችላል።

3.3.7 ትብብርን ለመግለጽ እያንዳንዱ የራስ አገዝ ቡድን ትንሽ መዋጮ ይከፍላል። ይህ ምናልባት የአሜሪካ ዶላር በማጠቀሙ አካባቢ ከሆነ በአመት 0-50 የአሜሪካ ሣንቲም ሊሆን ይችላል። የፈደሬሽኑ የአስተዳደር ወጭዎች በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በዋናነት ይሰባሰባል። አስፈላጊውን ለሚያሰባስቡት የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ፈደሬሽኑ እቅዱንና በጀቱን ያሣውቃቸዋል።

3.3.8 ፈደሬሽኑ ባስፈለገ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤውን ሊጠራ ይችላል። በተለምዶ ሁሉንም

3.3.9 የፈደሬሽኑን አመታዊ ሰራ ለመገምገም ጠቅላላ ጉባኤው በአመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። አሣታፊ የግምገማ መሣሪያዎች ስራ ላይ ይውላሉ። ለሂደቱ ምናልባትም የውጭ አመቻቾች በፌደሬሽኑ ሊቀጠር ይችላል።

3.3.10 ፌደረሽኑ ከረጂ ድርጅቱ፣ ከሌሎች አመቻቾች እና ባለሞያዎች ላገኘው አገልግሎት ክፍያ ይፈፅማል።

3.3.11 ብዙ አይነት የታቀዱ ስራዎችን ለመሰራት የፌደሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስራን መሠረት ያደረጉ ኮሚቴዎች ሊኖሩት ይችላሉ። ዋና ዋና ተግባሮችም

- የሕዝቡን ተቋም ዲሞክራሲያዊ አሠራር ለማረጋገጥ
- በኢኮኖሚ ማብቃት ላይ ጥሩ ሚና ለመጫዎት
- ፌደሬሽኑ የሕዝቡን ተቋም ለመሃበረሰብ ማብቃት ያደርሠዋል
- ፈደሬሽኑ ሕዝቡን ለፖለቲካ ብቃት ያመጣለታል

- ዋናው ሚና ነፃና ፍትሐዊ የሆነ መህበረሰብ በመፍጠር ለሁሉም አባላት ክብርና ስብእና መድረሱን ማረጋገጥ ነው፡፡

## 3.4 የፊደሬሽኑ ተግባራት ሊሆኑ የሚችሉ

- የፌደረሽኖችን ተግባር በእያንዳንዱ ፌደሬሽን እና በሚሠሩበት አካባቢ ሁኔታ ላይ የሚወሰን በመሆኑ አንዳንድ ሊሆን የሚችሉ ሁኔታዎች በልምድ ላይ ተመስርተው ተዘርዝረዋል፡፡ የፌደሬሽኖችን ተግባር መዘርዝር ከመጠን ያለፈ መተማመን ይሆናል፡፡
- በአጠቃላይ ፊደሬሽኑ አሠሣ በተደረበት ፍላጐት ላይ በመመስረት የተግባር አቅድ ያዘጋጃል፡፡ እነዚህ እቅዶች ለራሰ አገዝ ቡድኖች በተሰጡ ኃላፊነቶች፣ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት፣ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና በፌደሬሽኑ ንዑስ ኮሚቴዎች እንደሚሚሉ ይረጋገጣል፡፡ ፊደሬሽኑ ሊያከናውናቸው የሚችሉት ተግባራት በጥንካሬያቸውን የአካባቢው ሁኔታ በሚጠይቀው ሁኔታ ነው፡፡ ተግባሮችን የሚመሩት አንድ አንድ መርሆች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 3.4.1 የመሀበረሰቡን ፍላጐት የሚያሚሉ ተግባራት

- መሀበረሰቡን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በጤና ጉዳይ፣ በገበያ ጉዳይ፣ የተለያዩ የመንግስት አሠራሮች ወዘተ በተመለከተ የሚያገኙበትን የማሀበረሰብ የመረጃ መአከል ፊደሬሽኑ ሊያቋቁም ይችላሉ፡፡
- የማሀበረሰብ አባላቱ መጥተው ሙከራ የሚያደርጉባቸው እና መረጃ የሚያሠባሰቡባቸው ብዙ ትክክለኛ ቴክኖሎጂ ያላቸው አርአያ የሚሆኑ የመረጃ መአከላት ይኖረዋል፡፡
- ለአባላቶቹ እና ለማሀበረሰብ በግንኙነቶች ውሰጥ የዋስትና ሁኔታን ያመቻቻል፡፡ ይህ ዋስትና የጤና፣ የእህል እና አጠቃላይ ዋሰትና ሊሆን ይችላል፡፡
- ብዙ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤዎችን ለማዳበር ፊደሬሽኑ ጥሩ በሆነ ሁኔታ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ብዙሀን መገናኛን ይጠቀማል በዚህም አብዛኛውን ማሀበረሰብ መድረስ ይቻላል፡፡

- ፌደሬሽኑ በአባላቱና በመሀበረሰብ ተሣተፎ ከፍተኛ የሆነ የውሃ ጥበቃ ለማድረግ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡ ይህም እንደየተፋሰስ አስተዳደር እና ሰፊ የሆነ ስነምድራዊ ቦታን የሸፈነ የአካባቢ ስነምሕዳር ጥብቅ እርመጃዎች ነው፡፡

### 3.4.2 ሀይልና ተፅእኖ ፈጣሪነት ወሣኝ የሆኑበት ተግባራት

- ከፖሊስና ከፍትህ አሠራር ጋር በተፈጠረ እና በቆየ ግንኙነት ፍትህ ለተጓደለባቸው ሠለባዎች ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ፍትህ ማግኘታቸውን ፈደሬሽኑ ያረጋግጣል፡፡ የደካሞችን እና አቃፊ የሌላቸውን መሀበረሰቦች ጉዳይ ያሣውቃሉ፡፡
- ከአካባቢው የመንግስት አስተዳደሮች ጋር ቋሚ የሆነ ግንኙነት በመፈጠር እና እንደ መንግስት የረዘመ እጅ ሆኖ በክትባት ኘሮግራሞች፣ በነብስ አድን ተግባራት፣ በመሀይምነት ማጥፊትና ሰላምንና መረጋጋትን ማነሣሣት ላይ ይሰራል፡፡
- በከፍተኛ ደረጃ ከተመረጡ ተወካዮች ጋር ግንኙነት መፍጠረና ቀጣይ እንዲሆን ማድረግ

## 3.5 ለፌደሬሽኑ አቅም ግንባታ የሚሆኑ ግብአቶች

- ፈደሬሽኑ ሚናውን፣ ኃላፊነቱን እና ተግባሩን በትክክል ለመረዳት የፈደሬሽኑ አባላት የአቅም ግንባታ ግብአቶችን ይፈልጋሉ፡፡
- ለፈደሬሽን የሚሰጠው የአቅም ግንባታ ግብአት ከርዳታ ሰጪው ድርጅት ሃላፊነትን ለመቀበል እና የሕዝቡን ተቋም ስራ በትክክል ለማከናወን ይረዳዋል፡፡

የፈደሬሽን አባላት ከርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ኃላፊነትን የመቀበል እና መሀበረሰቡን መሠረት ያደረገ ድርጅት ሆኖ ለመቀጠል ሚናቸውን በግልጽ መረዳት አለባቸው፡፡ አንድን ድርጅት ለማስተዳደርና ለመምራት የአቅም ግንባታ ግብአት ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡

- የፌደሬሽን አባላት ኃላፊነታቸውን እና ሚናቸውን በተለይም በአሰአዊ መብት፣ የሕፃናት መብት እና በሴቶች መብት ዙሪያ ለማሟላት ይሰለጥናሉ፡፡
- የአቅም ግንባታ ግበአቶች ለቅስቀሣና ለጉትጎታ ይሰጣሉ፡፡
- የፌደሬሽን አባላት የገንዘብ አስተዳደር ጨምሮ የሕዝብ ተቋማት አስተዳደርን እና አመራርን ለማከናወን ግብአቶች ያስፈልጊቸዋል፡፡ በዚህ ዙሪያ የራሱን የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ብቃት ግምገማ ለማካሄድ እና ምክር ለመስጠት ለፈደሬሽኑ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ፈደሬሽኑ ፈንድ ለራስ አገዝ ቡድኖችና ለራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ለማስተላለፍ ስራ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ስለዚህ ይህን ለመምራት ክሕሎት ያስፈልጋል፡፡
- የራስ አገዝ ብድኖች ጥምረት ከሚያስተዳድሩት በላይ የሆኑ ኘሮጀክቶችን ለማስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኮማቴ እና ሌሎች ስራን መሠረት ያደረጉ ኮሚቴ አባላት ለኘሮጀክት አስተዳደርና በገንዘብ አሰተዳደር ዙሪያ ግብአቶች ይቀርቡላቸዋል፡፡ ይህ ማለት ፈደሬሽኑ በራሱ ይተገብራል ማለት ሳይሆን ለራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት እና ለራሰ አገዝ ቡድኖች የተሠጡ ስራዎችን በኮሚቴያቸው ውስጥ ክትትል ያደርጋል ለማለት ነው እንጂ፡፡
- ፍላጐት በመጣ ጊዜ ፈደሬሽኑ ሌሎች የአቅም ግንባታ ግብአቶችን ሊፈልግ ይችላል፡፡

ለፈደሬሽኑ የአቅም ግንባታ ግብአቶች የውጭ ሠው ጋር ውል ሊፈፀም ይችላል፡፡ ለተለያዩ የአቅም ግንባታ ፍላጐቶች ፈደሬሽኑ የባለሞያዎች የመረጃ ባንክ ሊኖረው ይገባል፡፡

### 3.6 በፌደሬሽን ደረጃ የራሰ ደሠሣ

ፈደሬሽኑ ራሱን የመዳሰስ፣ ብቃቱን የመከታተል እና ያስገኘውን ውጤት በጊዜው መገምገም አለበት፡፡

ፌደሬሽኑ በአመት አንድ ጊዜ ብቃቱን ሊዳሰስ ይችላል፡፡ በዚህ አሣታፊ ዳሠሣ ውስጥ የፈደሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና የፈደሬሽኑ አባላት ይሣተፋሉ፡፡ ዳሠሣው በውጤታማ እና በጊዜው የተደረሰባቸው የታቀዱ ተግባራት እና የፌደሬሽኑን ግብና አላማ በጠበቁ የሰራ እቅዶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

ፌደሬሽኑ በአመት አንድ ጉዜ ጠቅላላ ጉብኤ ይጠራል። በዚህ ስብሰባ ወቅት ፌዴሬሽኑ አመታዊ ሪፖርትና የሚቀጥለው አመት ዕቅዱን ያሣውቃል። እንደዚህም ጠቅላላ ጉባኤ አመታዊ ግምገማውን ያካሂዳል። አመታዊ ግምገማው ሲካሄድ በመተዳደሪያ ደንብ መሠረትና በአመጣው ውጤት ይሆናል።

## 3.7 ለፌዴሬሽኑ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች

በአንዳንድ ሁኔታዎች የተነሳ ቡድኑ በፌዴሬሽን ደረጃ መመስረት ባይችል ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን በዚህ ክፍል ተዘርዝሯል።

በተለያዩ ጥቂት ምክንያቶች ራሰ አዝ ቡድኑ በፌዴሬሽን ደረጃ ባይመሠረት እንኳን የራሱ የሆነ እሴትና አለማ ይኖረዋል።

- የማህበረሰብ ቁጥር ዝቅተኛ ሆኖ እስከ 100 ራሰ አገዝ ግሩኘ ወይም 8-10 የራስ አዝ ቡድን ጥምረቶች መመስረት ባይችሉ እንኳን ወደ ሕብረት መምጣት ይችላሉ።
- ባልተጠበቁ ምክንያቶች የሚረዳው ድርጅት ቢሮውን ቢዘጋ ወይም አካባቢውን ለቆ ቢወጣ ከመልቀቁ አስቀድሞ ጥቂት ራሰ አገዝ ቡድኖችን ለምሣሌ 15-20 እንዲሁም 1 ወይም 2 የራሰ አገዝ ቡድን ጥምረቶችን አቋቁሞ መውጣት አለበት
- የሚረዳው ድርጅት ከአላማው ወይም ከኘሮግራሙ አንፃር የተወሰነ የራስ አገዝ ቡድን ማቋቋም ቢፈለግ በትንሹ 10 ራስ አገዝ ቡድን ወይም አንድ የራስ አገዝ ቡድን ጥምረት መመሰረት አለበት።

## 4. የጊዜ ሰሌዳ

- በራስ አገዝ ቡድን ሃሣብ ውሰጥ ብዛት ጠቃሚ ነው በተለይ የማብቃት ሂደቱን ለማጠናከር ብዛት ወሳኝነት አለው። በአተገባበር ሂደት ውሰጥ ጥራትና መጠን እያመዛዘንን መሄድ መቻል አለብን። ራስን በራስ የመገምገሚያ መስኪያዎች በተለያዩ በሕዝባዊ ተቋማቶች ውስጥ ከዚህ በፊት ባለው ምዕራፍ ውስጥ እንዴት ማሣሳካት እንዳለበት ተገልፀዋል።
- በመጠን እንዴት እያደጉ እንዳሚሄዱ በዋናነት የሚያሳዩ ሂደቶችን በዚህ ክፍል ውሰጥ እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

### 3. ሂደቱን በመተግበር ሁኔታ ላይ ያሉ ደረጃዎች

| አመት | ደረጃ | የራአቡ ቁጥር | የራአቡጥ ቁጥር | ፌደሬሽን | የሰው ኃይል ግብአት |
|---|---|---|---|---|---|
| 0<br>0.5 | የሙከራ ጊዜ | 6 | | | 1 ኘሮጀክት ኦፊሰር<br>2 የማህበረሰብ አመቻች |
| 1<br>1.5<br>2<br>2.5 | የማስፋፊያ ጊዜ | 30 | 2 | | 1 ኘሮጀክት ኦፊሰር<br>4-6 የማህበረሰብ አመቻች |
| 3<br>3.5 | የማብቃት ደረጃ | 100 | 8 | ፌደሬሽን | 1ፒኦ 4-6 የማህበረሰብ አመቻች ቢያንስ 2 የማህበረሰብ አመቻች በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የሚታገዝ |
| 4<br>4.5 | ስራ የማቆሚያ ደረጃ | 150 | 12 | | 1ፒኦ 4-6 የማህበረሰብ አመቻች አብዛኞቹ የማህበረሰብ አመቻች በራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የሚታገዝ |

በሠንጠረዥ ውስጥ ያሉት ሂደቶች በ3 ደረጃዎች መካፋፈሉ ጠቀሜታ አለው፡፡ እነሱም የሙከራ ጊዜ፣ የማስፋፊያ ጊዜና የማጠቃለያ ወይም የማብቂያ ጊዜ ናቸው፡፡ በሠንጠረዥ ውስጥ ያሉት ሶስት ደረጃዎች መምጣት የሚፈለገውን የራሰ አገዝ ቡድን፣ የራስ አገዝ ቡድን ጥምረቶች እና የፌዴሬሽኑን ዕድገት የሚያሳይ ነው፡፡

**የማስፋፊያ ጊዜ** የጊዜው ሂደት ሁለት አመት ነው። ረጂው ድርጅት በዚህ የመስፋፉያ ጊዜ ውስጥ በጣም በአትኩሮትና በአንክሮ ሂደቶችን በመመልከት በመጀመሪያው የሙከራ ጊዜ ወይም 6 ወር የታዩ የአተገባበር ጉድለቶችን በመሙላት የሚሄድበት ጊዜ ነው።

የመከፋፊያ ጊዜ ቡድን የመመስረቱ መጠን በከፍተኛ እየጨመረ የሚፈለገውን ብዛት መድረስ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጥቂት የማህበረሰብ አመቻቾች መለየት ያለበት ጊዜ ነው። ቡድኑ ጥሩ የሚባሉ የማህበረሰብ አመቻቾችን ይይዛል። /መጀመሪያ ላይ ያሉትን 2 አመቻቾች በማካተት/

በዚህ ጊዜ ውስጥ ረጂው ድርጅትና የተቋቋሙ የራስ አገዝ ቡድን ለማህበረሰብ አመቻቾቹ ጥሩ ግንዛቤ በመስጠትና ከአመቻቾቹ ምን እንደሚጠበቅ ማስረዳት ያስፈልጋል።

**የሙከራ ጊዜ፡** የጊዜው ሂደት 6 ወር ሲሆን የሚነሳው ከመጀመያው የራሰ አገዝ ቡድን ምስረታ ጀምሮ ነው። እዚህ ደረጃ ላይ ሂደቱ ቀስ እያለ እንዲሄድ ይመረጣል ምክንያቱም ረጁው ድርጅት ሕዝብ/ ማህበረሰቡ የአደራጀጃቱ ሂደት ስላልተለመዱትና እንዲሁም ከተግባር የመማር ሂደቱ ቦታውን እስከሚይዝ ድረስ ይሆናል። በተጨማሪም ማህበረሰቡ ቡድን የመምስረቱ ጠቀሚታውን እስከሚረዱ ወይም እስኪቀበሉት ድረስ ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ ነው።

በዚህ ሙከራ ጊዜ ትክክለኛ የሆኑ የማህበረሰብ አመቻቾች የሚፈለጉበትና በቀጣይነት እንዲሄዱ ለማድረግ ይሄ ደረጃ ወሳኝነት ያለው ነው፡ ረጂው ድርጅት የማህበረሰብ አመቻቾች ከመምረጡ በፊት ሚናቸውና ኃላፊነታቸውን የሚረዳበት ጊዜ ነው። እንዲሁም ማህበረሰብ አመቻቾች ስራቸውን በአግባቡ ተረድተውና እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ሚያውቁበት ደረጃ ነው።

የማህበረሰብ አመቻቾች በየወሩ አንድ የራሰ አገዝ ቡድን ማቋቋምና እንዲሁም 4 የስልጠና ሞዴሎችን በማቅረብ በጥሩ ሂደት እንዲሄድ ማድረጊያ ዘዴ ነው። ከመጠን በላይ የሆነ የራሰ አገዝ ቡድን በዚህ ደረጃ አስፈላጊ አይደለም/ ወይም መወገድ አለበት።

ስለዚህ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ውሰጥ የርዳታ ሰጭ ድርጅቱ ተጨማሪ የማህበረሰብ አመቻቾችን ባሉት የራሰ አገዝ ቡድኖች አባላት በመታገዝ መለየት አለባቸው፡፡

በዚህ ደረጃ የተቀመጠው ግብ በዚህ አመት መጨረሻ ላይ 24 የራስ አገዝ ቡድኖች እንዲመሠረቱ ከዘህ በፊት ከተመሠረቱት ስድስተ በተጨማሪ እና በሁለተኛው አመት ሌላ 30 የራስ አገዝ ቡድኖች በመጨመር አጠቃላይ የራስ አገዝ ቡድኖች ቁጥር 60 ያደርሰዋል /6+24+30=60/፡፡ አንድ ጊዜ የራሰ አገዝ ቡድኖች ቁጥር አስር ከደረሰ የማህበረሰብ አመቻቾች የራሰ አገዝ ቡድኖቹን ለራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ፅንሰ ኀሣብ እና ስለመጀመሪያው የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት እንዲያደርጉ ሃሣባቸውን አትኮሮት ላይ ያደርጋሉ፡፡ በጊዜው የማህበረሰብ አመቻቾችን ከራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ፅንሰ ሃሣብ ጋር እንዲተዋወቁ እርዳታ ሠጭው መንግስታዊ ያልሆነ ድረጅት ቡድኑ የሚመሰረትበትን ፍጥነት ሁኔታ ግንዛቤ ቢኖረው በጣም ጥሩ ነው፡፡

አንደኛው የራስ አዝ ቡድኖች ጥምረት ተግባር ለአባል የራስ አገዝ ቡድኖች ክብካቤ ማድረግ እና አዳዲስ ቡድኖች መመስረት ነው፡፡ ስለዚህ ለማስፋፊያው በደረጃ ሁለተኛ አመት ቀድሞ የመተሰረተው የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት በተጨማሪም አዳዲስ የራሰ አገዝ ቡዱኖችን ይመሠረታል፡፡ ይህ እንግዲህ 60 የራሰ አገዝ ቡድኖች እና 5 የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ምስረታ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ነው፡፡ ቁጥሮቹ እንደገና አመላካቾች ናቸው፡፡ በአካባብው ሁኔታ ላይ መሠረት በማድረግ ትክክለኛው ቁጥር በትንሹ ሊያንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፡፡

**አቅም የመፈጠር ደረጃ፡** ይህ በግምት ለ3 አመት ጊዜ ይሆናል፡፡ የራስ አገዝ ቡድኖች ምስረታ እና የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ምስረታ ፍጥነት ሊቀጥል እና ከዚህ በላይም ሊጨምር ይችላል ብዙ እና በዙ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት እስከተመሠረቱ እና በቡድን ምስረታ እና በማጠናከር ላይ እስከተሣተፌ ድረስ፡፡

በዚህ ጊዜ ዋናው ስራ የሚሆነው ሚናዎችንና ኃላፊቶችን ከድጋፍ ሰጭ ድርጅቱ ወደ ሕዝቡ ተቋም ማስተላለፍ ነው፡፡

የፌደሬሽን ምስረታው ሌላ በጣም አስፈላጊ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ ፌደሬሽን የሚመሠረተው ወደ አንድ መቶ ገደማ የራስ አገዝ ቡድኖች ሊኖሩ እና ስምምነት ወይም ከዘያ በላይ የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሲኖሩ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ሂደቱ በተጀመረበት በአራት

አመታት ውስጥ ሊደረስበት ይችላል። የፌደሬሽን አቅም ግንባታ በረጅ ድርጅት ለሚቀጥለው አንድ አመት ራሱን ከስራዉ ለማውጣት በሂደት ላይ ባለበት በተመሣሣይ ጊዜ ይደረጋል። በ5 ወይም በ6 አመት ውስጥ ርዳታ ሰጭ ድርጅቱ ከስራው ውሰጥ ራሱን ሙሉ በሙሉ ማውጣት መቻል አለበት።

የማህበረሰብ አመቻቾች ቁጥር በምስረታ ጊዜ መጨመር የለበትም ከ4-6 እንደሆነ ይቆያል እንጂ። የመህበረሰብ አመቻቾች ቀስ በቀስ የሕዝብ ተቋም ስራዎችን ይስረክቧቸዋል። ይህ መተላለፍ የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ከተመሠረተ 6 ወር ከሆነው ጊዜ ጀምሮ ይጀመራል።

አዳዲስ የራስ አገዝ ቡድኖች እና የራሰ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ምስረታ ፌደሬሽን ከተመሠረተ በኂላ እና ድጋፍ ሰጭ ድረጅቱም ሰራውን ካቆመ በኂላም ይቀጥላል። ፊደሬሽኑ በተመሠረተበት ጊዜ 8 የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሊኖሩ ይችላሉ። ከሶስት አመታት በኂላ በፌደሬሽኑ ስር እስከ 15 የሚሆኑ የራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት ሊኖሩ ይችላሉ። የቁጥሩ እድገት ፌደሬሽኑ እስከፈለገ ድረስ ሊቀጥል ይችላል። በስነ ምድራዊ ሽፋን ወይም የአስተዳደር ድንበርን መሠረት በማድረግ ፌድሬሽኑ ለምስረታ ወሰን ሊያደርግ ይችላል ነገር ግን በሌላ መልኩ ደግሞ የዚህ መንገድ ጥንካሬ ሕዝቡ የሕዝቡን ተቋም ቀጣይነት ባለው መልኩ መቀላቀል ይችላል።